# ምዕራፍ ፬

## ኢትዮጵያ የወረሰቻቸው ያፅመ ርስት ይዞታዎቿ
## እና
## በእነዚህ ላይ ሳይቋረጥ የቀጠለው የጠላት እከይ!

ለቅዱሳት ኪዳናቱ፡ ባለአደራ የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ለረዥም ዘመናት፡ በፍጹም ነጻነት ጠብቆ ሊያኖራት ስለምን ፈለገ? እግዚአብሔር፡ ኢትዮጵያን፡ ያስቀመጣት፡ ለአብነት ሲኾን፡ አብነቷም፡ ባሁኑ ጊዜ፡ አይሉና ገንኖ፥ መረን ተለቅቆም በሚታየው፡ በሥጋዊው የዓለም አኗኗር ባህል አንጻር፡ ሌላ አማራጭ የኾነች፡ *የሕይወት መመሪያ ሥርዓት መኖርዋን፥* ይህችንም፡ መሰል የሌላትን መልካም ሕይወት፡ ማንኛውም ፈቃደኛ የኾነ ሰብአዊ ፍጡር፡ በዚች ምድር ላይ፡ *በእውነትና በመንፈስ* ሊኖራት የሚችል መኾኑን፡ ለእያንዳንዱ ግለሰብ፡ በገሃድ ማሳየት ነው፤ ይህን እውነታ፡ ራሱ፡ የዚችው፡ የሕይወት መመሪያ ሥርዓት፡ የህልውናዋ ባሕርይ አረጋግጦና አግዝፎ ያሳያል፤ ይህም፡ ከብዙዎቹ የመለኮት ምክንያቶች መካከል፡ አንዱ መኾኑን በማመልከት፡ ለዚህ ጥያቄ፡ ሃይማኖታዊ መልስ መስጠት ይቻላል።

### መልካሚቱ የሕይወት መመሪያ።

"ሕይወት፡ በመለኮት፤ ታሪክ፡ ለሰውነት፤ ኢትዮጵያ፡ በሰባቱ ኪዳናት፤ ኢትዮጵያዊው፡ ለእግዚአብሔር መንግሥት።" በሚሉ መፈክሮች፡ የተገለጸው፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ የአብነቷ ምሥጢር፡ ነፍሳቸው፡ በዚህ ዓለም፡ በፍርሃትና በጭንቀት፥ በሥጋትና በሁከት ተውጣ፥ ሥጋዊ ኑሮአቸው፡ የሲኦል ሥቃይ ለኾነባቸው የሰው ልጆች ኹሉ፡ ያለአንዳች ልዩነትና አድልዎ፡ ከእግዚአብሔር የቀረበላቸው፡ የአምላካዊ ግብዣ ጥሪ መኾኑን ያስገነዝባል። ይኸውም፡ እውነተኛው ረብኀና ጥቅም፥ ጣዕምና ትርጉም ያላትን፡ ያችን፡ *መልካም የሕይወት መመሪያ፡* ፈጣሪ፡ በቸርነቱ፡ እያንዳንዳቸው፡ በቀላሉ እንዲያውቋትና በነጻ እንዲያገኟት ስላደረጋት፡ እርሷን ተቀብለው፡ በእርሷ ለመኖር፡ ፈቃደኞች ይኾኑ ዘንድ፡ በብርቱ እንዲያመዛዝኑ የሚያሳስበው የአዋጅ ጥሪ ነው።

ያችን *የሕይወት መመሪያ* ለማግኘት፡ ለማናቸውም ሰው፡ በትምህርት፥ በሀብትና በሥልጣን ረገድ፡ ምንም ዓይነት፡ ደረጃ እንዲኖረው አላስፈለገም። የመጨረሻ በኾነው ያላዋቂነት፥ የድህነትና የውርደት ዐዘቅት ውስጥ ወድቀው የሚኖሩ ዕድለ ቢሶች እንኳ፡ ሊያገኟት የሚችሉበትን መንገድ፡ እግዚአብሔር አዘጋጅቷል። እርሷን ለማግኘት የሚያስፈልግ ነገር ቢኖር፡ ንጹሕና ትሑት የኾነ ልባዊ እምነት ብቻ ነው። እንዲያ ኾኖ ለመገኘት ደግሞ፡ ፍላጎቱ* ካለው፡ ራሱን ለማብቃት የማይችል፡ ማንም ሰብአዊ ፍጡር ከቶ የለም።

# ኢትዮጵያ፡

*ታሪክን በሚመለከት ደግሞ፡ "እኛ ራሳችን፡ የታሪክ ሠሪዎችና* ባለቤቶች ነን" ብለው የሚመኩትን፡ እኒያን የሰው ወገኖች ጨምሮ፡ ይህ፡ ፍጥረት የምንለው የእግዚአብሔር *ሥራ*፡ ማለትም፡ *መ*ላው ፍጥረተዓለም፡ በእርሱ፡ በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ *መ*ድረክ ላይ፡ የየራሳቸውን የተግባር ድርሻ የሚያከናውኑ ተዋናይያንና የመለኮታዊ ፈቃዱ፡ ፈጻሚ ባለወገኖች፥ የሕያዋን *ሥራ*ዎቹም *መ*ገለጫ አካሎች ኾነው የሚታዩበትና የሚመላለሱበት ግዙፍ አደባባይ ነው።

*ኢትዮጵያ፡ እንደአገርነት፥ ኢትዮጵያውያንም፡ እንደሕዝብነት፡ ዕድሜው፡ እጅግ ረዥም ለኾነ ዘመን፡ እስከዛሬ፡ በሕይወት የኖሩት፥ እንደቀሩትም ፍጡራን መሰሎቻቸው ሳይጠፉ፡ በህልውናቸው ሊቀጥሉ የቻሉት፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ወይም ለሌላ ዓላማ አይደለም። ዓላማውም፥ ምክንያቱም አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም፡ የእግዚአብሔር ሥራ የኾነችውንና በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት የተገለጸችውን እውነት፡ ማለትም፡ መለኮታዊቷን እውነት፡ በገሃድ እውን ለማድረግ፥ አጽንተው ለመጠበቅና ከትውልድ ወደትውልድ እያስተላለፉ፡ በሕያውነት ለማኖር መኾኑን አረጋግጠዋል።*

እግዚአብሔር፡ ከሰው ዘር ጋር ባደረጋቸው ቃል ኪዳናት ገዝፋ የታየችው፥ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊውም የሰውነት አካል ላይና ውስጥ፡ በሕያውነት የኖረችው፡ ይህች የእግዚአብሔር እውነት፡ ምንጊዜም የሰው ልጆች "ታሪክ" ኾና አታውቅም። ይኸውም፡ ያለፉትን የፍጡራንን ድርጊቶች ዜና መዋዕል ብቻ፡ በተለመደው አቀራረብ እንደሚያወጋው፡ እንደሰዎች ታሪክ አይደለችም ማለት ነው። ነገር ግን፡ በምድር ላይ በእውን ለተገለጹት፡ ለመለኮት የቸርነት *ሥራ*ዎች፡ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙም፡ ሕያው ማስረጃ ኾና፡ በዘለዓለማዊ ህልውናዋ ትቀጥላለች እንጂ።

በዚህ *መ*ሠረት፡ ኢትዮጵያ፡ በምድር ላይ፡ ለእግዚአብሔር *መ*ንግሥት፡ ሕያውት ምስክር ኾና፡ እስካሁን እንደቆየች ኹሉ፡ ወደፊትም፡ ይህንኑ አቋሟን አጽንታ፡ በእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብነታቸው፡ የዚችው *መ*ለኮታዊት *መ*ንግሥት ሕይወት ባለቤቶች ኾነው ከተገኙት ኢትዮጵያውያን ልጆቿ ጋር ትኖራለች።

እንግዴህ፡ ጉልህና እውን የኾነውን ይህን ነገር፡ በሰውኛ *መ*ንገድ ሲያስረዱት፡ እንዲህ በሚል ባጭር አገላለጽ፡ ተሥሎ ይገኛል፡- *የእያንዳንዱ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ሰውነት፥ ከዚህም የተነሣ፡ በዚህ መልእክት ውስጥ በተመለከተው ሃይማኖትና ምግባር ጸንቶ የሚኖረው፡ የማናቸውም እውነተኛ ክርስቲያን ሰውነት፡ ሰባቱን ቅዱሳት ኪዳናት፡ አጠቃልሎ የያዘ፡ የእግዚአብሔር ሕያው መጽሓፍና በምድር ላይ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሕያው መገለጫ ነው።*

የዓለሙ መፍረጃ!

# ኢትዮጵያ
# የዓለም መንግሥታትን
# ስትፋረድ!

እግዚአብሔር: ለመላው የሰው ዘር ህልውናና ተድላ ደስታ ሲል: በዚህ መልክና ሥርዓት: በምድር ላይ የመሠረታትን: የከበረች መንግሥቱን ለማፈራረስ: ዲያብሎስ የተባለው የሰይጣናትና የአጋንንት አለቃ: በሠራዊቱ አማካይነት የፈጸመውንና የሚፈጽመውን ተንኮልና ደባ: ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ እስካሁን ድረስ የነበረውና ዛሬም ያለው: እያንዳንዱ ሰብአዊ ትውልድ: የዓይን ምስክር ኾኖ ሲመለከተውና በራሱም ላይ እየደረሰ: ሲሠቃይበት ኖርዋል::

በስመ ጥፋው የአገዛዝ አቋሙ: በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ: "የክርስቶስ ተቃዋሚው" በሚል መለያ የሚታወቀውና በመለኮት አንደበት: "የሐሰት አባት" የተባለው: ይኸው: የክፋት ኹሉ ምንጭ የኾነው ዲያብሎስ: ይህንኑ የቀመለትን የማፈራረስ ዓላማ: ከግብ ለማድረስ ባለማቋረጥ የሚያደርገውን ሙከራ የሚያካሂደው: ሰውን ጨምሮ: ከፍጡራን መካከል በሚመርጣቸው አገልጋዮቹ መሣሪያነት መኾኑ ተረጋግጧል::

አገልጋዮቹ: ሰብአውያን ፍጡሮች በሚኾኑበት ጊዜ: እኒሁ ሰዎች: በዓለም ላይ በየትኛውም ቦታ: ሕጋዊነትንና ተቀባይነትን ለማግኘት ሲሉ: በማናቸውም የማስመሰል ዘዴና ረቂቅ ብልሃት ተጠቅመው: በሥጋዊዉም ኾነ በመንፈሳዊው ዘርፍ ያለውን በትረ ሥልጣን እስከመያዝ ይደርሳሉ:: በዚያን፣ ጊዜ: በዘመናቸው ያለው: የዚያ ትውልድ: የዓመፅና የክህደት ኃጢአቱ: ጽዋው ሞልቶ መፍሰሱና እግዚአብሔርም ያንን ትውልድ: ለሚጠብቀው ቅጣት አሳልፎ መስጠቱ ይታወቃል፤ዛሬ: በኢትዮጵያ እየተካሄደ እንደሚታየው ኹኔታ ማለት ነው::

በዚህ ረገድ: ከጥቂት ዓሥርተዓመታት በፊት: በእግዚአብሔር ዳኝነት: በግፈኞችና በዕብሪተኞች ላይ የወረደው: የኹለተኛው ዓለም ጦርነት መቅሠፍታዊ ዕልቂት: እዚህ ሊጠቀስ ይገባዋል:: ፋሺስት ጣልያን: ኢትዮጵያን በግፍ ወርራ እንድትይዝ: በምሥጢር ዶልተው: ያን ታላቅ በደል የፈጸሙት ሴረኞችና ተጠያቂዎች የነበሩት: ተቀማጭነቱ ጀኔቫ የነበረው: የመንግሥታት ማኅበርና እርሱን ይመሩት የነበሩት: የዘመኑ ኃያላን መንግሥታት: እንግሊዝና ፈረንሳይ: ምን ዓይነት የቅጣት ዋጋን እንደከፈሉ: በዛሬው: የመላው የሰው ልጅ ትውልድ ዘንድ ሳይቀር: ከአእምሮ የማይጠፋ: የቅርብ ጊዜ ትዝታ ሆኖ ሲታወስ ይኖራል::

እንደዚያ እንዳለፈው ኹሉ: ባሁኑም ጊዜ: በኢትዮጵያ ሰፍኖ የሚገኘው የመከራ ውርጅብኝና ወዳጅ አገሮች የተባሉት ሕዝቦች: እያንዳንዳቸው በየግላቸው፥ በጋራም: የአህጉራት ኅብረተሰብ በኾነው: በተባበሩት መንግሥታት ማኅበር አማካይነት: በኢትዮጵያ ላይ: ያለይሉኝታ: በገሃድ ሲፈጽሙት የሚታየው: የከዳተኝነት ድርጊት: እንደምልክት ኾኖ: ያን የቀደመውን የመሰለ ፍርድ እንዳያስከትል: ዛሬ ለሚኖረው: ለመላው የዓለም ሕዝብ: የሚያነቃና የሚያሳስብ: አዲስ የማስጠንቀቂያ ደወል ድምፅ ሊኾናቸው ይገባል::

ይህ፡ ንግርታዊና አሸባሪ የኾነው፡ የስምንተኛው ሺህ ዘመን፡ "የሰው ልጅ የህልውናው ፍጻሜ፡ እንዴት ይኾን?" ተብሎ፡ የዕድሉ ዓይነት፡ በአንክሮና በተዘክሮ የሚጠበቅበት ነው። እንዲህ ባለው ጊዜ፡ ብቸኛዪቱን ኢትዮጵያን፡ ከመኻከላቸው አግልለው፡ የበደል ድርጊታቸውን በመተባበር የሚያካሂዱባት አገሮች፡ የቀደመውን የሚመስል፡ መለኮታዊው የፍርድ ጊዜ ከመድረሱ በፊት፡ ለዚህ ጥሪ፡ ተገቢውን ምላሽ፡ ፈጥነው መስጠት ይኖርባቸዋል። በጊዜውም፡ የእግዚአብሔርን ምሕረት ያገኙ ዘንድ፡ በዚች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት በኾነችው ብሔረ አግዓዚት ላይ ያላቸውን የተዛባ አስተያየት ለማስተካከል፥ ስለሠሩትም በደል፡ በየበኩላቸው፡ እየራሳቸውን እንደገና በመመርመር፡ ንስሐ ለመግባት፡ በብርቱ አስበውበት፡ በዚህ ረገድ፡ የሚገባቸውን ግዳጅ እንዲፈጽሙ ያስፈልጋቸዋል።

አለዚያ፡ ይህ አካኼዳቸው፡ የሚያስከትለው ፍዳ፡ ካለፈው ይልቅ፡ እጅግ የባሰ አሠቃቂና ከመጨረሻው መደምሰስ የሚያደርስ፡ ጽኑ ይኾናል። ምክንያቱም፡ እዚህ ላይ፡ ቁምነገር ኾኖ የቀረበው ርእስ፡ ቀላል የኾነውን፡ የአንድን ግለሰብ፡ ወይም የዓለምአቀፍ ሰብአዊ መብትን የመተላለፍ፡ ወይም የየትኛውንም ዓይነት ሰብአዊ የሆነ የጽሑፍ ኪዳን ውል የማፍረስ ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥር የሚመራ ሕዝብ በሚኖርባትና በምድር ላይ፡ ለኹሉም የመለኮት ቃል ኪዳናት፡ የተቀደሰች ማኅደር በኾነችው፡ በኢትዮጵያ ላይ የተነጣጠረ፡ የዓመፅና የክህደት ፍላፃ ስለኾነ፡ *"እምከመ ርኢክሙ ትእምርተ ርኵስ ዘምዝባሬ፡ ዘተብህለ በዳንኤል ነቢይ"፡* ማለትም፡ *"በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን፡ የጥፋት ርኵሰት ምልክት በምታዩበት ጊዜ"* የሚለው፡ የራሱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢታዊ ቃል የሚፈጸምበት፡ ታላቅና አሳሳቢ ጉዳይ ነው እንጂ። አዎን! ከዚሁ ጥቅስ ጋር ተያይዞ የተነገረው የኢየሱስ ክርስቶስ[፲] የማስጠንቀቂያ ቃል፡ የማይታበል ነውና፡ ያለጥርጥር ይደርሳል።

ማነኛውም፡ *ሥጋዊ ኾነ ሃይማኖታዊ* አገርና ሕዝብ፡ በየግላቸውም ኾነ በቡድን ኾነው፡ ይህን የማስጠንቀቂያ ቃል ሰምተው ተገቢውን ለመፈጸም ፈቃደኛ ባይኾኑ፥ ወይም፡ ይባስ ብለው፡ ማስጠንቀቂያውን በመቃወም፡ የተቀደሰችውን አገር በማርከሱ እና/ወይም በማፈራረሱ ሴራ ውስጥ ተካፋይ በመኾን፡ በዚህ፡ የጥፋት ዓላማ የተጠመዱበትን ተግባር፡ በማናቸውም መንገድ በእምቢተኝነት ቢቀጥሉ፡ ያለጥርጥር፡ የሚጠብቃቸው ጽዋ፡ ዓይነቱና መጠኑ፡ ከዚህ በፊት ደርሶ ለማያውቅና ከላይ፡ ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው መቅሠፍት ለባሰ፡ ለሌላ እልቂት መዳረግ ብቻ ይኾናል።

## እውነተኛዋ ኢትዮጵያና
## እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን።

እንግዴህ፡ ይህ ነው፡ ኢትዮጵያውያን፡ በሕዝብነት አንድ የኾኑባት ኢትዮጵያ፡ በዚህ ዓለም በገሃድ ተገልጻ፡ ከአዳምና ሔዋን የፍጥረት ጊዜ አንሥቶ፡ እስከዚች እስከዛሬዋ ቀን ድረስ የኖረችና ወደፊትም በዚህ ህልውናዋ ለዘለዓለም የምትቀጥል የእግዚአብሔር መንግሥት ለመኾን ያበቃት።

"ጋላ" የሚለው ቃል፡ ለማናቸውም ግለሰብ ወይም ጎሣ የሚሰጥ፡ የግብር ስም እንጂ፡ ለተለየ ግለሰብ ወይም ጎሣ የተሰጠ የተጸውዖ ስም አይደለም። ቀድሞ፡ በዘመነ አሪት፡ ያልተገረዘ፥ ቀጥሎም፡ በዘመነ ክርስትና፡ ያልተጠመቀ ወገን ኹሉ፡ "ጋላ" ይባላል፤ ስለዚህ፡ በዛፍ ላይ ይደረግ የነበረውን፡ ያን የመሰለውን አምልኮ ይፈጽሙ የነበሩት ወገኖች፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ዘንድ፡ "ጋሎች" እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት፡ ከዚሁ አምልኳቸው የተነሣ እንደነበረ ሊታወቅ ይገባል። ኋላ ግን፡ እነዚያ ወገኖች፡ ፍጥረተ ዓለሙን ኹሉ በፈጠረው፡ በአንድ እግዚአብሔር አምልኮ ላይ የተመሠረተውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት እየተማሩና እያወቁ፡ በፈቃዳቸው ሲገረዙና ሲጠመቁ፡ "ዐምሓራ" ወይም "ክርስቲያን" እየተባሉ፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ኾኑ! በኢትዮጵያዊነታቸውም፡ ኢትዮጵያን፡ ይኸው እስከዛሬ፡ "ኢትዮጵያ" አሰኝተዋት ኖሩ! እነሆ፡ ዛሬም ይኖራሉ። እነርሱም፡ ራሳችንን፡ "ኢትዮጵያውያን ነን" ብለን አምነን፡ ይህን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ ሃይማኖት አድርገን፥ ኢትዮጵያ በምትባለው፡ በዚች አገር፡ አንድ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኾነን የምንኖረው፡ እኛው ነን።

በአሁኑ ጊዜ ግን፡ ራሳቸውን፡ እንደአንድ የተለየ ብሔረሰብ በመቁጠር፥ መጠሪያቸውንም፡ ቀድሞ፡ በአሞ ወንዝ አካባቢ ሠፍረው በነበሩት፡ በጥንቶቹ ነዋሪዎች መታወቂያ፡ "ወረ አሞ"፥ በዛሬው ሕዝባዊ አነጋገር ደግሞ፡ "ወሮሞ" ወይም "አሮሞ" ብለው በመሠየም፡ ማንነታቸውን ለይተው፡ መጓዝ የጀመሩት ወገኖች፡ ይህን የመሰለው አምልኮ፡ በኢትዮጵያ እንሠራርቶ እንዲቀጥል የሚፈልጉ መኾናቸውን፡ እነሆ በድርጊታቸው እንመለከታለን። ይኹን እንጂ፡ የእነዚህ ወገኖች፡ አባቶችና እናቶች ቀደም ብለው፡ ከፍተኛ መሥዋዕትነትን በመክፈል፡ ለኢትዮጵያዊነት ዓላማ የፈጸሙትን ታላቅ ሙያና ያበረከቱትን ዘለዓለማዊ ፍሬ፡ እስቲ ለአንድ አፍታ መለስ ብለን በማስተዋል እንመልከተው! ይህም፡ በጥንቱ ጊዜ፡ በዚህ ረገድ፡ በመለኮታዊው ምሥጢርና ኃይል የተከናወነውን ዕፁብ ድንቅ ሥራ የሚያስታውስ ነው።

የዚህ ብሔረሰብ አባል የኾነ ማናቸውም ግለሰብ፡ ወንድ ወይም ሴት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ሲያምን፡ እየተጠመቀ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ፡ ቀደም ብለው የነበሩት፡ ሌሎቹ ብሔረ ሰቦች፥ አሮሞው ጭምር፡ ተስማምተው በመሠረቱትና በሚኖሩበት፡ የኢትዮጵያዊነት ኅብረተሰብ ውስጥ አባል ይኾናል። ያም፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ላይ የተመሠረተው ኢትዮጵያዊነት፡ ለዚያ ግለሰብ፡ በቅድሚያ የሚያረጋግጥለት፡ እርሱ፡ በቋንቋው፡ "ዋቃ" እያለ፡ በዛፍ ያመልከው የነበረው፡ የዛፉና የሌላው ፍጥረት፥ የራሱም የሰው ፈጣሪ የኾነው፡ "እግዚአብሔር ወልድ"፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሰው ኾኖ ተወልዶና ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ፡ ፍጥረቱን፡ በተለይም፡ በመልኩ የፈጠረውን፡ የሰውን ዘር፡ በሙሉ ያዳነ መኾኑን ነው፤ ከዚያ ቀጥሎ፡ ለዚሁ፡ "ሰው" ለተባለው ፍጡሩ፡ እርሱ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ አጐናጽፎት ከነበረው፡ ከመልካሙ የገነት ሕይወት፡ አሸፍቶና አስወጥቶ፥ በባዕድ አምልኮም አሥሮ ከሚያሠቃየው፡ ከዲያብሎስ የጭካኔ አገዛዝ፡ ማለትም፡ ከክፋት፥ ከኃጢአትና ከሞት ነጻ ያወጣው መኾኑን ያረጋግጥለታል፤ በመጨረሻም፡ ያ ግለሰብ፡ በዚህ ዓለም በሚያሳልፈው ምድራዊ ኑሮው፡ ጥላቻና ጦርነት የሌለበትን፡ የሰላምና የብልፅግና ዕድሜን፥ በሚመጣውም ዓለም፡ የዘለዓለምን ሕይወት ያወረሰው መኾኑን ያስተማምንለታል።

"ጋላ" የሚለው ቃል፡ ለማናቸውም ግለሰብ ወይም ጎሣ የሚሰጥ፡ የግብር ስም እንጂ፡ ለተለየ ግለሰብ ወይም ጎሣ የተሰጠ የተጸውዖ ስም አይደለም፡፡ ቀድሞ፡ በዘመነ ኦሪት፡ ያልተገረዘ፥ ቀጥሎም፡ በዘመነ ክርስትና፡ ያልተጠመቀ ወገን ኹሉ፡ "ጋላ" ይባላል፤ ስለዚህ፡ በዛፍ ላይ ይደረግ የነበረውን፡ ያን የመሰለውን አምልኮ ይፈጽሙ የነበሩት ወገኖች፡ በቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ዘንድ፡ "ጋሎች" እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት፡ ከዚሁ አምልኳቸው የተነሣ እንደነበረ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ኋላ ግን፡ እነዚያ ወገኖች፡ ፍጥረተ ዓለሙን ኹሉ በፈጠረው፡ በአንድ እግዚአብሔር አምልኮ ላይ የተመሠረተውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖት እየተማሩና እያወቁ፡ በፈቃዳቸው ሲገረዙና ሲጠመቁ፡ "ዐምሐራ" ወይም "ክርስቲያን" እየተባሉ፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ኾኑ! በኢትዮጵያዊነታቸውም፡ ኢትዮጵያን፡ ይኸው እስከዛሬ፡ "ኢትዮጵያ" አሰኝተዋት ኖሩ! እነሆ፡ ዛሬም ይኖራሉ፡፡ እነርሱም፡ ራሳችንን፡ "ኢትዮጵያውያን ነን" ብለን አምነን፡ ይህን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ ሃይማኖት አድርገን፥ ኢትዮጵያ በምትባለው፡ በዚች አገር፡ አንድ፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኾነን የምንኖረው፡ እኛው ነን፡፡

በአሁኑ ጊዜ ግን፡ ራሳቸውን፡ እንደአንድ የተለየ ብሔረሰብ በመቁጠር፥ መጠሪያቸውንም፡ ቀድሞ፡ በአሞ ወንዝ አካባቢ ሠፍረው በነበሩት፡ በጥንቶቹ ነዋሪዎች መታወቂያ፡ "ወረ አሞ"፥ በዛሬው ሕዝባዊ አነጋገር ደግሞ፡ "ወሮሞ" ወይም "ኦሮሞ" ብለው በመሠየም፡ ማንነታቸውን ለይተው፡ መጓዝ የጀመሩት ወገኖች፡ ይህን የመሰለው አምልኮ፡ በኢትዮጵያ እንሠራርቶ እንዲቀጥል የሚፈልጉ መኾናቸውን፡ እነሆ በድርጊታቸው እንመለከታለን፡፡ ይኹን እንጂ፡ የእነዚህ ወገኖች፡ አባቶችና እናቶች ቀደም ብለው፡ ከፍተኛ መሥዋዕትነትን በመክፈል፡ ለኢትዮጵያዊነት ዓላማ የፈጸሙትን ታላቅ ሙያና ያበረከቱትን ዘለዓለማዊ ፍሬ፡ እስቲ ለአንድ አፍታ መለስ ብለን በማስተዋል እንመልከተው! ይህም፡ በጥንቱ ጊዜ፡ በዚህ ረገድ፡ በመለኮታዊው ምሥጢርና ኃይል የተከናወነውን ዕፁብ ድንቅ ሥራ የሚያስታውስ ነው፡፡

የዚህ ብሔረሰብ አባል የኾነ ማናቸውም ግለሰብ፡ ወንድ ወይም ሴት፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ሲያምን፡ እየተጠመቀ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ፡ ቀደም ብለው የነበሩት፡ ሌሎቹ ብሔረ ሰቦች፥ ኦሮሞው ጭምር፡ ተስማምተው በመሠረቱትና በሚኖሩበት፡ የኢትዮጵያዊነት ኅብረተሰብ ውስጥ አባል ይኾናል፡፡ ያም፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ላይ የተመሠረተው ኢትዮጵያዊነት፡ ለዚያ ግለሰብ፡ በቅድሚያ የሚያረጋግጥለት፡ እርሱ፡ በቋንቋው፡ "ዋቃ" እያለ፡ በዛፍ ያመልከው የነበረው፡ የዛፉና የሌላው ፍጥረት፥ የራሱም የሰው ፈጣሪ የኾነው፡ "እግዚአብሔር ወልድ"፡ በመጨረሻው ዘመን፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ሰው ኾኖ ተወልዶና ኢየሱስ ክርስቶስ ተብሎ፡ ፍጥረቱን፡ በተለይም፡ በመልኩ የፈጠረውን፡ የሰውን ዘር፡ በሙሉ ያዳነ መኾኑን ነው፤ ከዚያ ቀጥሎ፡ ለዚሁ፡ "ሰው" ለተባለው ፍጡሩ፡ እርሱ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ አጐናጽፎት ከነበረው፡ ከመልካሙ የገነት ሕይወት፡ አሸፍቶና አስወጥቶ፥ በባዕድ አምልኮም አሥሮ ከሚያሠቃየው፡ ከዲያብሎስ የጭካኔ አገዛዝ፡ ማለትም፡ ከክፋት፥ ከኃጢአትና ከሞት ነጻ ያወጣው መኾኑን ያረጋግጥለታል፤ በመጨረሻም፡ ያ ግለሰብ፡ በዚህ ዓለም በሚያሳልፈው ምድራዊ ኑሮው፡ ጥላቻና ጠርነት የሌለበትን፡ የሰላምና የብልፅግና ዕድሜን፥ በሚመጣውም ዓለም፡ የዘለዓለምን ሕይወት ያወረሰው መኾኑን ያስተማምንለታል፡፡

ለዚህም፡ የቅርቦቹን፡ ጥቂቶች አባቶቻችንን ለአብነት ብንጠቅስ፡ እነአጼ በካፋ፥ እነራስ አሊ፥ እነራስ ጎበና፥ እነፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፥ እነደጃዝማች ባልቻ፥ እነአለቃ ደስታ ነገዎ፥ እነደጃዝማች በቀለ ወያ፥ እነደጃዝማች ገረሱ ዱኪ፥ እነጦር አዝማች (General ጄኔራል) ሙሉጌታ ቡሊ፥ እነደጃዝማች ክፍሌ ዳዲ፥ እነጦር አዝማች ጃገማ ኬሎ፥ እነጦር አዝማች ወልደ ሥላሴ በረካ፥ እነፊታውራሪ ዓባይነህ ፊኖና እነፊታውራሪ ሩጋ አሻሜ፡ ከሌሎቹ፡ ከብዙዎቹ መካከል፡ ለኢትዮጵያዊው ማንነት፡ አንጸባራቂ ከዋክብት ኾነው የሚቀርቡ፡ የኢትዮጵያ ታማኞች ልጆች ናቸው።

ታዲያ! እኒህና እነርሱን የመሰሉት፡ የቀሩት፡ ስመ ጥሩዎች ጀግኖች አባቶቹ፡ በየሰላሙ ጊዜ ኾነ፡ በየጦርነቱ ወቅት፡ በኢትዮጵያዊነታቸው፡ ለኢትዮጵያ፡ በመሥዋዕትነት፡ የፈጸሙት ታላቅ ያገልግሎት ሙያ፡ ወደር የሌለው፥ ዛሬ ላለውና ለመጪዎቹም የኢትዮጵያ ትውልዶች፡ እንዲህ፡ በአርአያነት ሲጠቀስ የሚኖር መኾኑ እየታወቀ፡ በአሁኑ ዘመን የሚገኘው የኦሮሞው ብሔረሰብ አመራር፡ የያዘው አዝማሚያ ሲታይ፡ እንኳንስ፡ በሕይወተ ሥጋ ቆመውና በሕይወተ ነፍስ ኾነው፡ ድርጊቱን ለሚመለከቱት፡ ለእነርሱና እነርሱን ለመሰሉት፡ ላሉትና ላለፉት ቀርቶ፡ ሕያው ታሪካቸውን ለሚያውቅ፡ ባዕድ ተመልካች እንኳ፡ የቱን ያህል ያሳዝን? በእነዚያ አባቶቹና እናቶቹ እውን ኾኖ የተከሠተውን፥ በዚህም መጽሐፍ ውስጥ የተብራራውን፥ በዓለም ሕዝቦች መካከል፡ እንደማራቶኑ ሩጫ፡ ያለውን ቀዳሚ ሥፍራ እንዲይዝ፡ በሚያኮራ መልክ የሚያረጋግጥለትን ኢትዮጵያዊነቱን ትቶ፡ በሌላ ማንነት ለመተካት፡ እየተከተለ ያለውን መንገድ ሲያዩት፡ ምንኛ ያስለቅስ?

ይህ ኹሉ ሲኾን፡ እኒያን፡ አባ መላን (ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን) የመሰሉት፡ ጉምቱዎቹና በሳሎቹ ሽማግሌዎች ወዴት ኼዱ? በብልህነታቸውና በነገር ስልት አዋቂነታቸው፡ "ቆይ! ይዋል፡ ይደር!" እያሉ፡ ከባዱን ጉዳይ፡ እንዲቃለል፥ ውስብስቡም ችግር፡ መፍትሔ እንዲያገኝ የማድረግ፡ የተፈጥሮ ችሎታ ያላቸው አዛውንቶችስ፡ ወዴት ነው ያሉት? ፋሺስት ጣልያን፡ እንዲህ እንደዛሬው፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ፡ በጎሣና በቋንቋ ሊለያይ የተበተበውን መረብ በዘረጋበት ጊዜ፡ በፋሺስቱ ገዥ ፊት፡ ነጭ ጤፍና ጥቁር ጤፍ አስመጥተው፡ በአውድማ ላይ ለየብቻ በማፍሰስ ካሳዩት በኋላ፡ ቀጥሎ፡ ኹለቱም ዓይነት ጤፍ እንዲደባለቅ አድርገው፡ "በል፡ እስቲ አሁን፡ ነጩንና ጥቁሩን ጤፍ ለይልኝ!" ባሉት ጊዜ፡ ጣልያናዊው ገዥ፡ "አይቻለኝም!" ስላላቸው፡ "ይኸውልህ! ኢትዮጵያዊ ማለት ይህ ነው!" ብለው፡ ለእውነት ሲሉ፡ ሳይፈሩ፡ ራሳቸውን ለሞት መሥዋዕትነት እስከማቅረብ የደረሱ፡ ይህን ዓይነቱን ሙያ የፈጸሙ፡ አባ ጅፋርን የመሰሉ፡ ያገር ቀንደኞች፡ ዛሬ የሉም ማለት ነውን?

"በሕይወተ ሥጋ ብቻ ሳይኾን፡ በሕይወተ ነፍስም፡ አንለያይም" በማለት፡ "ቀሪው ሥጋዬ፡ ከአጼዬ፡ ከምኒልክ አጠገብ ይረፍልኝ!" የሚለው ቃላቸው የተፈጸመላቸው፡ የመጀመሪያው የአጼ ምኒልክ፡ የጦር ምሉክ (Ministre ሚኒስትር) ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፥ ከእርሳቸውና ከሌሎቹ ታማኞች ኢትዮጵያውያን ጀግኖችም ጋር፡ የጣልያንን ጦር፡ አድዋ ላይ ድል ያደረጉት፡ ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ፡ ዛሬ ከየመቃብሮቻቸው፡ ብድግ ብለው፡ እየተካኼደ ያለውን ጉድ ቢያዩ፡ ምን ይሉ?

የዓለሙ መፋረጃ!

ፋሺስት ጣልያን: በማይጨው ጦር ሜዳ ላይ ድል አድርጎ: ወደአዲስ አበባ መገሥገሡን ሲሰሙ: ከሽምግልና መከዳቸው: እንደጉልማሳ ብድግ ብለው በመፎከር: "አሁን: ከአጼዬ ከምኒልክ ፊት: (በሕይወተ ነፍስ) ቀርቤ ሲጠይቁኝ: ምን ብዬ ልመልስ ነው? አድዋ ላይ ድል ያደረግነው: የዘር ጠላታችን: የጣልያን ጦር: 'ማይጨው ላይ እንዴት ኾነ?' ብለው ቢጠይቁኝ: ምን መልስ ልሰጣቸው ነው? 'አሸንፎ: ኢትዮጵያን ወረረ!' ልላቸው ነውን? አይታሰብም! ና! ጋሻ ጦሬን ስጠኝ! ጉራዴዬን አስታጥቀኝ! ፈረሴን ጫን!" ብለው: ለዘመቻ ተነሥተው ጠላትን የተጋፈጡትና በቾ ውስጥ: አበቤ በሚባለው ሥፍራ: ለኢትዮጵያዊነታቸው የተሠዉት: እኚሁ: ባልቻ አባ ነፍሶ አይደሉምን?

"ኢትዮጵያ" የሚለው ያገሪቱ ሕያው ስም: "ኦሮምያ፥ ዐማራ፥ ትግራይ፥ አፋር፥ የደቡብ ሕዝብ፥ ...ወዘተ." በሚለው የከፍፍሉሽ ስም፥ እንዲሁም አረንጓዴ: ብጫ: ቀይ የኾነው ሰንደቅ ዓላማ: "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለው: ማኅተሙ ከላዩ ተሠርዞ: በሌላ ምልክት መተካቱ ብቻ ሳይኾን: ራሱም: የሦስቱ ቀለማት ሰንደቅ ዓላማ: በተለያዩ: የከፍፍል ሰንደቅ ዐላማዎች ሊተካ ሲሞከር፥ "አዲስ አበባ" የሚለው የመናገሻ ከተማዋ ስም: ወትሮ: በእነእቴጌ ጣይቱ ጊዜ: ፊን ፊን ስትል ለታየቻው የፍልውሃ ምንጭ: "ፊንፊኔ" የሚል ስያሜ መሰጠቱ ተዘንግቶ: ቃሉ: የሌላ ጎሣ ቋንቋ ይመስል: "'ፊንፊኔ' መባል አለበት" ሲባል፥ ይልቁንም: ለኢትዮጵያውያን ነጻ ሕዝብነትና ጥንታዊነት ልዩ መታወቂያ የኾነው፥ በዓለም ላይ ቅድሚያ ያለውና በአፍሪቃ: ብቸኛ የኾነው: ኢትዮጵያኛው የግእዝ ፊደል: በተለይ: በኦሮሞው ብሔረሰብ ዘንድ የማይፈለግ ኾኖ: ለሌሎች ሕዝቦች: የቅኝ ተገዢነት ማረጋገጫ በኾነውና Latin (ላቲን) በሚባለው: በደመኛው ጠላታቸው: በጣልያን ፊደል መተካቱን ሲያዩ: ከቶ ምን ይገርማቸው? የቱንስ ያህል ያሳዝናቸው?

በእውነተኛ ሰውነታቸው ምክንያት: ለከፍተኛ የታማኝነት አደራና የኃላፊነት ማዕርግ የበቁት: እኚህ: ኹለት ስመጥር ኢትዮጵያውያን ጀግኖች: ኢትዮጵያዊነት: ምን ዓይነት ጸጋን የሚያስገኝ፥ የቱን ያህል የከበረና ከኹሉ በላይ የላቀ የሕይወት አቋም መኾኑን በማረጋገጥ: በመካከላቸው የተለዋወጧቸው ሕያዋን ቃላት: በተለይ ለዛሬው ትውልድ ታላቅ አርአያነት ያለውን መመሪያ ትተው ያለፉ በመኾናቸው: እነዚያን ቃላት: እዚህ ላይ: ለአብነት ጠቅሻቸዋለሁ::

ይኸውም: ከዕለታት አንድ ቀን: እኚሁ: ኹለት: መኳንንት: ወደየትውልድ አካባቢያቸው አብረው እየተጓዙ ሳሉ: ቀድሞ: በአጼ ምኒልክ ሠራዊት ድል ኾነው እተማረኩበት ቦታ ሲደርሱ: ደጃዝማች ባልቻ: "ይኸውልዎ ጌታዬ! ይኼ እኮ ነው: የተማረክንበት ሥፍራ!" ብለው: ለፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ እያመለከቱ ሲያስታውሷቸው: "ይተዉ እንጂ ደጃዝማች! የተባረክንበት ነው!"[፲፭] ብለው: ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የመለሱላቸው ቃል ነው::

## ኢትዮጵያ
## ትውልዷን ስትፋረድ!

ይህች ኢትዮጵያ፡ በዘመነ ብሉይም ኾነ በዘመነ ሐዲስ፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ በየዘመናቱ፡ ሕዝቧ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ በሚፈጽመው በደል ምክንያት፡ በአረማውያን ሳይቀር፡ አልፎ አልፎ እየተወረረች፡ በባዕዳን አገዛዝ ሥር የቆየችባቸው አጫጭር ጊዜያት እንደነበሩ ይታወቃል። ይኹን እንጂ፡ እኒህን በመሰሉ ውድቀቶች ውስጥ በመገኘቷ፣ ይህም ማለት፡ ባሁኑ ጊዜ፡ በሃይማኖት አልባው፡ ሕዝባዊ አገዛዝ፣ ቀደም ብሎ በነበረውም፡ በደርግ የጋርዮሽ አገዛዝ፣ እንዲሁም፡ በፋሺስት ጣልያን የወረራ አገዛዝ፣ ከዚያ በፊትም፡ በአሕመድ ግራኝ፡ የሰይፍ አገዛዝ፣ እጅግ ርቆም፡ በአይሁዳዊቷ ጉዲት፡ የጭካኔ አገዛዝ ቀምበር ሥር እየወደቀች፡ የቅጣት ጊዜያትን ያሳለፈች በመኾኗ ብቻ፡ ኢትዮጵያ፡ በእነዚያ ዘመናት፡ "ማንነቷንና ምንነቷን ለውጣ ገዢዎቿን መስላ ነበር፣ ወይም የእነርሱን እምነትና አመራር ተቀብላ፡ እንደነርሱ ኾና ነበር!" ማለት አይደለም። በእነዚያ ዘመናት፡ ህልውናዋን፡ በፈተና ማዕበልና በመከራ መካከል አሳለፈች ማለት ነው እንጂ።

እንደእነዚያ ጊዜያት ኹሉ፡ በአሁኑ ጊዜም፡ በሰዎች አስተሳሰብ፡ የአገር ውስጥ ወገኖችን መሣሪያ በማድረግ፡ የቅዱሱን ኪዳን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ ቀስ ብሎ፡ በረቀቀ መንገድ ለማጥፋት፡ በሥውር እየተካኼደ የቆየው ዓለም አቀፍ ሰይጣናዊ ሴራ፡ በበለጠ እየተከሠተና እየጎላ ሲፈጸም ይታያል። ይህንኑም፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ሊያውቁትና ሊገነዘቡት፣ ቢቻላቸውም፡ በሃይማኖታዊ ምግባር፡ ተገቢውን ጥንቃቄና መከላከል ሊያደርጉ ይገባቸዋል። ያም ባይኾን፡ "አጠፋፋቸውን እያወቁት እንጂ፡ ሳያውቁት እንዳይኾን ቢኾን ይሻላቸዋል!" በማለት፡ እንደሚከተለው ቀርቦላቸዋል።

### ሦስቱ የቀሩ ሕያዋን ውርሶች።

ተመልከቱ! ኢትዮጵያን፡ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያውያንንም፡ ኢትዮጵያውያን የሚያሰኟቸው፡ በዚህ፡ በአንደኛው፡ የመጽሐፉ ክፍል ውስጥ የታተቱትና በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ላይ የተመሠረቱት ቁም ነገሮች፡ አብዛኞዎቹ፡ ከነምልክቶቻቸው፡ በኢትዮጵያ ምድር ላይ፡ በሕዝባዊና በመንግሥታዊ ይፋ፡ መታየታቸው እየቀረ እንዲኼድ፡ መደረግ ከተጀመረ፡ ዓመታት እየተቆጠሩ እንዳለፉ፡ ዓለሙ ኹሉ፡ በይፋ የሚያውቀው ነው። ደብዛቸው አልጠፋ ብሎ፡ ለሴረኞቹ ያስቸገሩና በቀላሉ፡ በሦስት አርእስት ሊጠቃለሉ የሚችሉ፡ የዝክረ ነገር ማኅተሞች ግን፡ ገና በሕያውነት ሲንቀሳቀሱ ይታያሉ! እነዚህም፡ "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም፣ የግእዝ ፊደልንና አኀዙን የያዘው "ኢትዮጵያኛ" የሚባለው የዐማርኛ ቋንቋ እና *"ምአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው ምልክት ተነሥቶ ባዕድ የኾነው የተተካበት፡ አረንጓዴ፡ ብጫ፡ ቀይ የኾነው ሰንደቅ ዓላማ ናቸው።

## ኢትዮጵያ፡

እግዚአብሔርማ! እያንዳንዱ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚለውን፡ ወንዱንም፥ ሴቱንም፡ ምን እንደሚያደርግ፡ ዝም ብሎ፡ በትዝብት እየተመለከተ፥ ቀኑም ሲደርስ፡ ለእያንዳንዱ፡ ዋጋውን የሚከፍልበትን፡ ቁናውን እየሰፋ፡ የራሱ መለኮታዊ ዕቅድ ምን እንደኾነ፡ ዕፁብ ድንቅ በኾነ ጥበቡ፡ ፈለጉን፡ ለዓለሙ ኹሉ በይፋ እያሳየ ነው:: ዕፁብ ድንቅ በኾነ ጥበቡ፡ በዚህ ረገድ፡ በቅርቡ የፈጸመውንም ትንግርት፡ እስቲ በማስተዋል እንመልከትለት!

አዎን! ሴረኞቹ፡ የሥልጣኑም፥ የሀብቱም፥ የጥበቡም፡ ሰጪና አዳይ፡ እርሱ እግዚአብሔር መኾኑን ክደው፡ "እኛ ነን ባለቤቶቹ" ብለው፡ በኃይላቸው፥ በገንዘባቸውና በእውቀታቸው በመመካት፥ የተቀደሰ ስሙን ላለማንሣትም በመወሰን፡ በራሳቸው በሚታበዩበት ጊዜ፡ እግዚአብሔር ደግሞ፡ እነርሱን ሊያሳፍር፡ እነማንን፡ አንሥቶ፡ እንዴት ስሙን እንዳስጠራ፥ እነዚያን እንዲጠፉ በሰዎች ሴራ የተፈረደባቸውን፡ ሦስቱን መለኮታውያን ማኅተሞቹን፡ መታደግ ብቻ ሳይኾን፡ እንዴት እንዳገነናቸው፡ በሚበቃ ተመለከትን እኮ! መመልከት ብቻ ሳይኾን፡ እየራሳችንም፡ የጣፋጩ ፍሬ ተሳታፊዎች ኾነን፡ የተአምራቱን በዓል፡ በያለንበት አላከበርንምንዴ!?

እግዚአብሔር የዚህን ዕቅዱን ፈለግ ለመግለጥ፡ መሣሪያዎቹ ይኾኑ ዘንድ የጠራቸውና ያከበራቸው፥ በሴረኞቹ ዘንድ፡ "ደካሞች፥ ደኾችና መሃይሞች" ተብለው የተናቁት፡ እኒያ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቹ፡ እነማን ናቸው?

በሰዎች ጥበብ ሠልጥነው ከተዘጋጁት፡ ከመላው ዓለም ምርጦች ጋር ለመወዳደር፡ ወደሰልፉ ሜዳ ለመኼድ በተነሡበት ቀን፡ ማተባቸውን በአንገታቸው ላይ አሥረው፡ "እግዚአብሔር ቢረዳን! የእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢኾን!" እያሉ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር የተቀደሰ ስሙ እንዳይጠራ በተከለከለባቸውና የብዙኃን መገናኛ በኾኑት፡ በብሔራዊው የዜና ማሠራጫ አውታሮች፡ የተቀደሰ ስሙን፡ በሃይማኖታዊ ስሜት፡ ደጋግመው በማውሳት፡ የጠሩት እነማን ናቸው?

የሩጫ ኃይል፡ በሰው ትምህርት ሳይኾን፡ ከእርሱ እግዚአብሔር ብቻ፡ በተፈጥሮ የሚሰጥ ጸጋ ስለኾነ፡ በዚያ ኃይል፡ ተሽቀዳድመው፡ አሸናፊዎች በመኾን፡ ዓለምን "ጉድ!" በሚያሰኘው ቃል፡ አፉን ይዞ እንዲደነቅና እንዲገረም ያደረጉት እነማን ናቸው?

እንደጢስ ተንነው፥ እንደጉም በንነው እንዲጠፉ የተፈረደባቸው፡ "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም፥ በቀስተ ደመና ምልክት፡ "አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ" የኾነው፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ፥ እና "ዐማርኛ" የሚባለው ኢትዮጵያኛው ባለፊደል ቋንቋ፡ እነዚህ ሕያዋን፡ የእግዚአብሔር ጸጋዎች፡ በዚህ ድል አድራጊነታቸው፡ በመላው ዓለም ላይና በመላው የሰው ዘር መካከል፡ ማንነታቸውና ምንነታቸው፡ በበለጠ ታውቆ፡ ዝናቸው እንደገና እንዲያበራና እንዲያንፀባርቅ ያደረጉት እነማን ናቸው?

በቅርቡ፡ በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. በሲድኒ፡ የአውስትራልያ ከተማ በተካሄደው፡ "አልምፒያድ" በተባለው፡ ዓለም-አቀፍ የጨዋታ ትእይንት ላይ፡ የድል አክሊሎችን የተቀዳጁት፡ ኃይሌ ገብረ ሥላሴ፥ ደራርቱ ቱሉ፥ ሚሊዮን ወልዴና ገዛኸኝ አበራ፥ እንዲሁም፡ ጌጤ ዋሚ፥ ደምሴ ቶላና ሌሎችም አይደሉምን? ታዲያ፡ እነዚህ እነማን ናቸው?

የዓለሙ መፋረጃ!

እንኳንስ ኢትዮጵያውያን: መላው ዓለም ያወቃቸው ስለኾኑ: ስለእነርሱ ማንነት: እኔ: እዚህ ላይ: የማክለው: ምንም ዓይነት ሓተታ ሊኖረኝ አይችልም:: ብቻ! የእግዚአብሔር መንፈስ: በእነርሱ ላይ አድሮ: ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን: ስለፈጸመው ተአምራዊ ኃይል: ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት: ያደረባቸውንና የተሰማቸውን: የጋለ ኢትዮጵያዊ ስሜት: ለጀግኖቹ የኢትዮጵያ ልጆች: ባደረጉላቸው የተጥለቀለቀ አቀባበል: በሚበቃ ገልጸውታል::

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን አምላክ: ኢየሱስ ክርስቶስ: ከነእናቱ ድንግል ማርያም ጋር: በቃል ኪዳኑ: ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን: በቸርነቱ የሚሠራው ተአምርና ኃይል እየቀጠለ የሚኼድ መኾኑን: በዚህ ድርጊቱ: ለሴረኞቹና ለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ በድጋሚ አረጋግጧል::

## የኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ አንድነት: እውነተኞች ምሳሌዎች::

ይህ ኹኔታ: ዛሬ ብቻ ሳይኾን: ኢትዮጵያ ባሳለፈችው የህልውና ዕድሜዋ: በየዘመናቱ: እየተከሠተ ታይቷል:: እጅግ ቅርብ በኾነው ጊዜ የደረሰውን: አንዱን የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫ: መልካም ፍሬ: እዚህ ላይ በምሳሌነት: እጠቅሰዋለሁ:: ይኸውም: እንደዛሬው ኹሉ: እኒያ ሦስት የቅዱሱ ኪዳን ማኅተሞች: እንዲደመሰሱ: ኃያላኑ: የኢትዮጵያ የዘር ጠላቶች: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን መሣርያ በማድረግና ከአገር ውስጥ ተፃራሪዎችዋ ጋር በመመሣጠር ያካኼዱት: ረቂቅና ግዙፍ ዘመቻ: እንዴት ተንኮታኩቶ እንደወደቀ፥ የኢትዮጵያ የኾነው የተቀደሰ ዓላማ ግን: እንዴት ለፍሬ እንደበቃ በሰልፉ ሜዳ ላይና በዚያ በተገኘው የድል ውጤት: እንዴት ለፍሬ እንደበቃ የተረጋገጠበት: ኤርትራ: ወደእናት አገሩዋ እቅፍ የተመለሰችበት የገድል ዜና መዋዕል ነው::

የኢትዮጵያ ልጆች የኾኑት: የአንድነት ታጋዮች ኤርትራውያን: ከኢትዮጵያ ጋር በፍጹም አንድነት ለመዋሃድ: በታላቅ የሀገር ፍቅርና በቆራጥ የሃይማኖት ጀግንነት የተነሡ መኾናቸውንና "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም፥ "ኢትዮጵያዊነት"ም: በምንም መንገድ ሊሻሩ ወይም ሊለወጡ የማይቻል መኾኑን: "ኢትዮጵያ ወይም ሞት!" በሚል መፈክራቸው አረጋግጠዋል!

ቀጥለውም: ገና በትግሉ ጊዜ: ቋንቋን በሚመለከት: "ዓረብኛና ጣልያንኛ: ለእኛ ለኤርትራውያን: የባዕድ ቋንቋዎች ናቸው፤ በተለይ: ጣልያንኛ: ከቁም ነገሩ ውስጥ ተጠቅሶ ማየቴ: እጅግ አሳዝኖኛል:: ...ፈጣሪ ይመስገን: የተባበሩት መንግሥታት: ለእኛ ለኤርትራውያን: ባዘጋጀልን የአስተዳደር ሕግ: ከእናታችን ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መኾናችንን አረጋግጦልናል፤ ኹላችንም: የአንዲት ኢትዮጵያ ዜጎች መኾናችን: በሕግ ተወስኖልናል::

"ስለዚህ፡ የውስጥ አስተዳደራችን ቋንቋ፡ ትግርኛ ኾኖ፡ የሱታፌ (federal ፌዴራል) መንግሥታችን የኢትዮጵያ መሥሪያ ቋንቋ የኾነው ዐማርኛ ቢገባ፡ የተባበሩት መንግሥታት ከሰጠው ውሳኔ ጋር የሚስማማ ስለኾነ፡ ሓሳቤ እንዲመዘገብልኝ እጠይቃለሁ።" ሲሉ፡ በአንድነቱ ታጋዮች ስም፡ አንዱ መሪ፡ ኳላ "ንቡረ እድ" የተባሉት፡ መላከ ሰላም ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም፡ የተናገሩት ቃል፡ ለተነሣንበት አርእስተ ነገር፡ በቂ ማስረጃ ኾኖ የሚቀርብ ነው።

በመጨረሻም፡ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በሚመለከት፡ ብዙ ማተት ይቻላል፤ ነገር ግን፡ ባጭሩ፡ የኤርትራ ሕዝብ፡ የቅኝ ገዢዎቹን ቀምበር ተሸክሞ ባሳለፋቸው ዘመናት፡ በዚሁ ሰንደቅ ዓላማው ምክንያት፡ ይደርስበትና ይፈጸምበት የነበረውን ግፍ የሚያሳየውን አንዱን ወገን ብቻ በመጥቀስ ማጠቃለሉ ይበቃል፤ ይኸውም፡ ለኃዘኑም ኾነ ለደስታው፡ የኢትዮጵያዊነት ስሜቱን የሚገልጸው፡ አረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ የኾነውን፡ ይህንኑ ሰንደቅ ዓላማውን አንግቦ በሚፈጽመው ሥርዓቱ ነው። ሰው ሲሞት፡ የአስከሬኑ ሣጥን የሚጎናጸፈው፥ ሠርግና ልዩ ልዩ የኀብረተሰብ በዓል በሚፈጸምበት አዳራሽ ወይም ዳስ ውስጥ፡ ተዘርግቶ ድምቀት እንዲሰጥ የሚደረገው፡ ይኸው ሰንደቅ ዓላማ ነው።

"ይህን ሰንደቅ ዓላማ ለምን ይዛችሁ ታያችሁ?" እያሉ፡ የቅኝ ገዢዎችና የፋሽስት ጣልያን ወታደሮች፡ ሕዝቡን በሚያሠቃዩበት ጊዜ፡ የሕዝቡ መልስ፡ "እነዚህ፡ ሦስቱ ኀብረ ቀለማት፡ የሃይማኖታችን ምልክቶች ስለኾኑ፡ አንለውጣቸውም!" የሚል እንደነበረና በዚህ የድፍረት ትግላቸው፡ ከመካከላቸው፡ ብዙዎቹ፡ ከፍተኛ መጉላላት ይደርስባቸው እንደነበረ፡ በዝክረ ነገራቸው ተመዝግቧል። በተለይ፡ የአንድነቱ ትግል በተፋፋመበት ወራት፡ ስማቸው ከላይ የተጠቀሰው፡ የታጋዮቹ መሪ፡ "እኛ ኤርትራውያን፡ ዕድሜያችንን ሙሉ፡ ሥቃይ ስንቀበልና ስንሠዋ የኖርነው፡ ለማን ነው? ...ለኢትዮጵያዊነት ምልክታችን፥ ለአረንጓዴ፥ ብጫ፥ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን አልነበረምወይ? ...ሕይወታችን አድርገን፡ የምናመልክባትን፡ ሰንደቅ ዓላማችንን ይዘን፡ ለምን የመንግሥት መሪነቱን ሥልጣን፡ ሌሎች አይረከቡትም? ...ለእኛ፡ ከኹሉም የምትበልጥብን፡ ኢትዮጵያዊቷ ሰንደቅ ዓላማችን ስለኾነች፡ ለጊዜያዊ ሥልጣን አንለውጣትም!" ብለው የተናገሩት[፲፮ ሀ] ቃል፡ ሕያው ማስረጃ ኾኖ፡ ሲነገር ይኖራል።

\+ \+ \+

# ምዕራፍ ፩

## ምክርና ማስጠንቀቂያ::

ይድረስ: በመላዋ ምድር ላይ ለምትኖሩ: የክርስትና፥ የይሁድናና የእስልምና፥ እንዲሁም: የሌሎች ሃይማኖቶችና እምነቶች ተከታዮች ለኾናችሁ ሕዝቦች! መንፈሳውያንና ሥጋውያን መሪዎች! የዓለም መንግሥታትና የአህጉራት ድርጅቶች ኹሉ!

"ሰላም ለእናንተ ይኹን!" እያልሁ: ይህን: የማቀርብላችሁን መልእክት: አዳምጣችሁ እንድትቀበሉኝ እለምናችኋለሁ::

ይህችን "ኢትዮጵያ"ን በሚመለከት: ስለሚኖራችሁ የአስተያየት ዝንባሌና የአቋም መመሪያ: ትጠነቀቁ ዘንድ አደራ እላችኋለሁ! ስለየራሳችሁ ደኅንነትና በጐነት ስትሉ: ከኢትዮጵያ ጋር ያላችሁ ግንኙነት: በምን ዓይነት አካሄድ ላይ እንደሚገኝ: እንደገና ትመረምሩት ዘንድ፥ ትገመግሙትም ዘንድ አሳስባችኋለሁ! ስሑታን በኾኑ: ሰብአውያን አስተሳሰቦች ተታልላችሁ፥ ግዱፋን በኾኑ የፍጡራን ስሌቶችም ተማርካችሁ: በዚህች አገር ላይ ተፃራሪ የኾነ ተግባር ለመፈጸም አስባችሁ እንደኾነ: በንስሐ ተመለሱ!

እዚህ ላይ: "ለምን?" ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር: እስካሁን እንደተብራራው: "ኢትዮጵያ: በምድር: የእግዚአብሔር መንግሥት ስለኾነች ነው" የሚል ምላሽን ያገኛል:: አዎን! ፈጣሪ: በራሱና ለሰው ዘር ተጠሪዎች ለመኾን በበቁት አበው መካከል ለተካየዳቸው ለሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት: ባለአደራ ጠባቂ፥ የታመነች ማኅደርና ሕያው ምስክር ኾና ለመኖር' መቻልዋ: ይህችን አገር: እንዲህ ለመኾን አብቅቷታል:: ስለዚህ: በዚህ ህልውናዋ መቀጠል ይኖርባታል ማለት ነው::

እንግዴህ: ይህን መልእክት ተቀብሎና አክብሮ አለመፈጸም: በእግዚአብሔር ላይ በተቃውሞ እንደመነሣት፥ ይህም: ባጭር ቃል ሲነገር: ፀረ እግዚአብሔር እንደመኾን ያስቆጥራል! ምናልባት: ይህን መልእክት በሚቃረን ዓላማ ላይ ተመሥርቶ: በተግባራዊነት የሚካሄድ አመራር ካላችሁ: ለደኅንነታችሁ ስትሉ: ያን አካሄዳችሁን አቃንታችሁ የምትመለሱበትን መንገድ እንድታስቡ እለምናችኋለሁ::

### ኹለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳይረሳ!

ኹለተኛውን የዓለም ጦርነት አትርሱት! በዚያን ጊዜ: አስገዳጅ ሥልጣን ያላቸው ጥቂት ኃያላን አህጉርና የዓለም መንግሥታት ማኅበር የተባለው ድርጅት ከፈጸሙት የማናለብኝነትና የግዴለሽነት ድርጊት የተነሣ: በዘመኑ የነበረው ትውልድ: በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ: እስካሁን ወደር ያልተገኘለትን: እጅግ መራራ የኾነ ዋጋን ከፍሎ እንደነበረ አስታውሱ! ያ መቅሠፍታዊ ቅጣት: በዚያ ትውልድ ላይ የወረደበት እኮ: እንደዛሬው ኹሉ: በዘመኑ የነበሩት: አጼ ኃይለ ሥላሴ: በግንባር ተገኝተው ያቀረቡለትን የምክርና የማስጠንቀቂያ መልእክት: በዕብሪት ንቆና አቃሎ ሳይቀበል በመቅረቱ እንደነበረ ታውቃላችሁ!

ከዚህ ጋር፡ ተጨማሪ ትምህርትና አጥጋቢ ማስረጃ ይኾናችሁ ዘንድ፡ ራሱ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፡ እንዲቀበል በተፈረደበት ፍዳ ተይዞ፡ እስከዚች አፍታ ድረስ እየተሠቃየበት ያለውን መርገም፡ በማስተዋል ተመልከቱት! በእርስ በርስ ጦርነት፥ በተለያየ የደዌ ቸነፈር፥ በረሀብ አለንጋ፥ በስደትና የአውሬ ራት በመኾን፥ በሌላም መልክ፡ እየቀጠለ የኼደውንና የሚኼደውን፡ የእልቂቱን መጠን፡ ይኸው ታዩታላችሁ!

ታዲያ፥ ለዚህ ፍዳ የዳረገው ጠንቅ፡ ከቶ ምን ይመስላችኋል? ገና ቀደም ብሎ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመንና ከዚያም በኋላ የተሰጠውን፡ ይህንኑ፡ ዛሬ፡ ለእናንተ የቀረበውን የመሰለውን፡ የምክርና የማስጠንቀቂያ መልእክት "አልቀበልም!" በማለቱና፡ እስካሁን በእምቢተኛነቱ በመጽናቱ አይደለምን?

ስለዚህ፡ እናንተም፡ ይህን ከመሰለው መርገምና መቅሠፍት ትድኑ ዘንድ፡ ዕድሉ ሳያመልጣችሁ፥ ጊዜውም ሳይመሽባችሁ፡ እባካችሁ፡ ፈጥናችሁ፡ ይህን ምክርና ማስጠንቀቂያ ተቀበሉ!

## ንስሓ! እምጻኤ ፍሥሓ!

ይህን ምክርና ማስጠንቀቂያ መቀበላችሁን የምታረጋግጡት፡ ከዚህ የሚከተሉትን የእውነት ምግባሮች፡ በቅደም ተከተል በመፈጸም ይኾናል፡፡ ይኸውም፡ በቅድሚያ፡ እያንዳንዳችሁ፡ በየግል ሰውነታችሁ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁ ግንኙነት፡ እንዴት እንደኾነ፡ በተመሥጦ ታመዛዝናላችሁ፤ ከዚያ፡ እየራሳችሁን፡ ከእግዚአብሔር ጋር በንስሓ ታስታርቃላችሁ፤ በዚህ ጊዜ፡ በየውስጣችሁ የዕርቅና የሰላም መንፈስ ይኾንላችኋል፤ የተፈጥሮ ወገናችሁ ከኾነውም፡ ከማንኛውም ሰው ጋር ዕርቅና ሰላም የማድረግ ኃይል ይሰጣችኋል፤ በመጨረሻ፡ በዓለሙ ኹኔታ ውስጥ፡ እያንዳንዳችሁ ያለባችሁ ግዳጅ፥ ኃላፊነትና ተጠያቂነት፡ ምን እንደኾነ፡ በጥልቅ ከመመርመር ትደርሳላችሁ፤ ከዚህም የተነሣ፡ ማናቸውንም ችግር፡ በቀላሉ ለማስወገድ የሚያስችላችሁን፡ እውነተኛ መፍትሔ፡ በግልም ኾነ በጋራ፡ ወይም በኅብረት ታገኛላችሁ!

ይህም ኹሉ፡ እግዚአብሔር፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም፡ ለፍጥረተ ዓለሙ በሰጠው፡ የምሕረት ቃል ኪዳን ይከናወንላችኋል!

እንግዴህ፡ ይህ መልእክት ለተላለፈላችሁ፡ ለእናንተ፡ ክርስቲያኖችና ክርስቲያን ላልኾናችሁ፥ እንዲሁም፡ ለኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያን ላልኾናችሁ ኹሉ፡ ይህን እላለሁ! ኹሉ፡ በእርሱ ፈቃድ እየተመራ፡ መልካም ከኾነው ፍጻሜ ይደርስ ዘንድ፡ ኹላችን ለምናምንበትና ለምናመልከው፡ ለአንዱ እግዚአብሔር፡ ኹላችሁ፡ በስሙ፡ ንስሓ እንድትገቡ፥ ይህም ማለት፡ የእርሱን የእውነት መንገድ ከሚጻረር፡ የክፋት አካሄዳችሁ እንድትመለሱ አሳስባችኋለሁ፡፡

አዋቂና ብልህ ከሚባለው ሕያው ፍጥረት መካከል፡ በዓይነትም ኾነ በብዛት፡ ላቅ ያለውን ደረጃ የያዝነው፡ እኛ፡ በእግዚአብሔር መልክ ተፈጥረናል ብለን የምናምነው፡ የሰው ዘር ወገኖች መኾናችን፡ በኹላችንም ዘንድ እሙን ነው፡፡

## የዓለሙ መፋረጃ!

እንዲህ እንደመኾናችንም፡ ባሳለፍነው፡ በረዥሙ የህልውና ዘመናችን ኹሉ፡ የቀደሙትና የዛሬዎቹ ትውልዶቻችን፡ የፈጸሟቸው፡ ከፉም ኾኑ ደጋግ ድርጊቶች፡ ካስገኙልን የሕይወት ልምዶች መካከል፡ በመቀጣጫነት የሚያገለግለንን፡ ዋና ዋናውን እንኳ፡ በትምህርትነቱ ቀስመን በመጠቀም፡ በምድር ላይ፡ ማንነታችን እንዲታወቅበት፡ ተወስኖ የተሰጠንን የመኖር ዕድልና የዕድሜ ጸጋ፡ የተሻለና የሠመረ እናደርገው ዘንድ፡ ከፍጥረታችን ባለቤት፡ ያለማቋረጥ ሲጠበቅብን ቆይቷል።

በተለይም፡ ባለፉት ኹለት ሺህ ዓመታት ውስጥ፡ በግል፥ በአገርና በአህጉር አቀፍ ደረጃ፡ አስተማማኝና ዘለቄታነት ያለውን፡ የሰላም፥ የዕድገትና የብልጽግና አኗኗር ማስገኘት የሚቻልበት መንገድ፡ የትኛው እንደኾነ፡ ለእኛ ለሰው ልጆች፡ ማወቅ ቢሣነንም፡ እግዚአብሔር፡ በብዙ የተለያየ መልክ ማስተማሩን አላቋረጠም። እርሱም፡ የመለኮትን እውነት በመከተል ብቻ የሚደረስበት ነው። የሰው ልጅግ፡ ትክክለኛው መንገድ፡ በአብዛኛው ዓለም ዘንድ፡ እስካሁን ታምኖበት፡ ሲሠራበት እንደሚታየው፡ የተራቀቀ ሰብአዊ ፈሊጥ፥ የተከማቸ የሀብት ይዞታና የተደራጀ የጦር ኃይል፡ እነዚህ ሦስቱ የአገር አውታሮች፡ ተሟልተው፥ ተቀነባብረውና ተከናውነው የሚካሄዱበት መንግሥታዊ አቋም መስሎት፡ በድካም ሲዋትት ይታያል።

ታዲያ፥ ያቺ የመለኮት እውነት የት ትገኛለች? የመለኮት እውነት፡ ራሱ እግዚአብሔር ነው! እርሱም፡ በመልኩ በፈጠረው አካል፡ ሰው ኾኖ፡ በዘመኑ መጨረሻ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ተገለጸ። ኢየሱስ ክርስቶስም፡ ምሉዕ በኵለሄ በኾነው በመንፈስ ቅዱስ ማንየዊነት፡ ህልውናው፡ እስከዛሬ ቀጥሏል፤ ዛሬም እየቀጠለ ነው፤ ለወደፊትም ይቀትላል።

እንደሚታወቀው፡ የሰው ዘር፡ በምድር ላይ፡ ፍጹሟን ሕይወት፡ በግለሰብ፥ በአገረሰብና በዓለም ኅብረተሰብ ደረጃ ሳይቀር፡ በእጁ አስገብቶ ሊሰፍንባት፡ በሥጋ በኖረበት ዘመን ኹሉ፡ በምኞት መቃጠል ብቻ ሳይኾን፡ ጣርና ጋር ባልተለየው ታላቅ ትግል፡ የተሟሟተበትና ዛሬም የሚጋደልበት ዓላማው መኾኑ፡ እነሆ በገሃድ ይታያል። ነገር ግን፡ ከዚህ ዓላማው ለመድረስ፡ እስካሁን አልተቻለውም፤ ወደፊትም አይቻለውም።

ስለዚህ፡ ፈጣሪያችን፡ ይህን ኹሉ ያደረገው፡ የዘለዓለም ሰላም፥ ዕድገትና ብልጽግና ተሟልተው ወደሚገኙባት፡ ወደዚች ፍጹም ሕይወት መርታ የምታደርስ፡ አንዲት ብቸኛ መንገድ መኖርዋንና እርሷም፡ ያችው የመለኮት እውነት ብቻ መኾኗን፡ በቀላሉ ሊያሳምነን እንደኾነ መረዳቱ አያዳግተንም።

ይህችም መልእክት የተላከችላችሁ፡ ራሱ የመለኮት እውነት ከኾነው፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም፡ የአዳምና የሔዋን፥ የኖኅና የመልከ ጼዴቅ፥ የአብርሃምና የሙሴ፥ የዳዊትና የማክዳ አምላክ ሲኾን፡ በትንቢቱ የፍጻሜ ዘመን፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" ተብላ፡ የሰውን ዘር ከምትወክለው፥ ከጽዮናና ከኢትዮጵያዊቷ፥ ከፍጥረተ ዓለሙም ንግሥት፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመወለድ፡ በሰውነት የተገለጸውና ራሱም፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ፥ ካህኑ ለዓለም፥ ንጉሠ ጽዮን ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" ተብሎ፡ በመላው ፍጥረተ ዓለሙ ላይ የነገሠው ነው።

\+ \+ \+

# ምዕራፍ ፯

## የኢትዮጵያውያን የቅዱሱ ኪዳን ጸሎቶች።

### የሃይማኖት ጸሎታቸው።

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ ኹሉን በያዘ፥ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የአብ ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን፡ የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል፥ ኹሉ በእርሱ የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፥ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ ሥጋ፥ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡ ፍጹም ሰውን ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱም ቀኝ፡ በዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። ለመንግሥቱ ፍጻሜ የለውም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከአብ የሠረፀና በነቢያት አድሮ የተናገረው፥ በሐዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፥ እናመሰግነዋለንም።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባዔ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን።

ኀጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

የሙታንን መነሣት፥ የሚመጣውንም ሕይወት ተስፋ እናደርጋለን። ለዘለዓለሙ፥ አሜን።

## ለእግዚአብሔር የሚቀርብ፡

## የምስጋና ጸሎታቸው፡፡

አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! "እናንተ ስትጸልዩ፡ "አቡነ ዘበሰማያት" በሉ!" ብሎ፡ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትህልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምህልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን፡፡ ስለዚህ እናመሰግንሃለን፡፡

ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን፡፡ ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ፡ በምድርም የምትኖር ኾንህ፡፡ ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ፡፡ መንግሥትህም መጣችልን፡፡ በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም እንዲሁ ኾነ፡፡ የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜያችን ኹሉ የሚያስፈልገንን ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን፡፡

ለዘለዓለም ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንን፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን፡፡ በእርሱም፡ ኀጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን፡፡ እኛም የበደሉንን ኹሉ፡ እንዲሁ ይቅር እንድንል አስቻልኸን፡፡ ያንተ ልጆች ለመኾን የምንበቃበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን፡፡ ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፥ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን፡፡

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል፡ ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን፡፡

"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" በተባለው፡ በንጉሣችን በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፥ ኀጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተስፋ ቃልህ እንጠብቃለን፡፡

ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም ያንተ ናቸው፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

የዓለሙ መፋረጃ!

## ለድንግል ማርያም የሚቀርብ፡

## የሰላምታ ጸሎታቸው፡፡

እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን፡፡ በአሳብሽ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም ድንግል ነሽ፡፡ በዚህ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡

ማኅጸንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ፡፡ ቀድሞ በነቢያት፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የተባልሽ፥ እኛም፡ "እምነ ጽዮን" ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር፡ ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ፡፡ እግዚአብሔር አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳኑ ምሕረቱን ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ "ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ" እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን፡፡

በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንቺ ለእኛ፡ የአደራ እናታችን፥ እኛም ለአንቺ፡ የአደራ ልጆችሽ ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ፡ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም እንደማይለየን እናምናለን፡፡

ይህን ያደረገ፡ ቸሩ አባታችንን፡ ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን፤ ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

\+ + +

# ምዕራፍ ፯

## ለመኾኑ፡ "የዚች የእግዚአብሔር እውነት ልኡክ ነኝ" የሚለው እርሱ፡ ማነው?

የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው ኢትዮጵያ፡ ልጇ፥ አገልጋይዋና መልእክተኛዋ የኾንሁት እኔ፡ ለዚህ የአገልግሎት ጥሪ ያበቃኝ ምን እንደኾነ፡ ለአንባቢ ለመግለጽ፡ ዜና መዋዕሌን፡ ባጭር፡ እንደሚከተለው አስታውቃለሁ፡፡

ስሜ፡- ኤርምያስ ከበደ ወልደኢየሱስ፥ ማዕርጌ፡ መጀመሪያ፡ "ቄስ"፥ ኋላ፡ (የአኵስም ጽዮን) "ንቡረ እድ" ነው፡፡ (ስለአኵስም ጽዮን ንቡረ እድነት፡ ማብራሪያው፡ በገጽ ፩፻፲፱-፩፻፳፪ ላይ ይገኛል፡፡)

ልደቴ፡ በሓምሌ ፫ ቀን፥ ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ፥ አዲስ አበባ መናገሻ ከተማ፥ ኢትዮጵያ ነው፡፡

ትምህርትን የቀሠምሁት፥ ክህነትንም የተቀበልሁት፡ በጸጋ እግዚአብሔር፡ በአገሬ በኢትዮጵያ ነው፡፡

ጋብቻዬን፡ ከወይዘሪት ራሔል ዘካርያስ ጋር፡ በሓምሌ ፫ ቀን፥ ፲፱፻፵፰ ዓ. ም. በሃይማኖታዊ ሥርዓት በመፈጸም፡ የመሠረትነውን የትዳር ሕይወት፡ እግዚአብሔር፡ በሕፃንነቷ ከጠራት፡ ከተምኔተና በ፲፱፻፺፩ ዓ. ም. በሞተ ሥጋ ከተለየን፡ ከትንቢተ ጋር፡ መልእክተ፥ ትምህርተ፥ ስብከተ፥ ሃይማኖተ፥ ሰማዕተና ስብሐተ በተባሉ፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ባርኮናል፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ አገሬ ኢትዮጵያ፡ ባሏት፡ ሦስት የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ እየተዘዋወርኩ፡ ባለቤቴ፡ ወይዘሮ ራሔል ዘካርያስም፡ እርሷን በሚመለከታት የኃላፊነት ድርሻዋ ሳትለየኝ በመሥራት፡ ኹለታችንም፡ በዚህ ረገድ፡ ያለብንን ግዳጅ አከናውነናል፡፡

ይህም፡ የመለኮታዊቷ መንግሥት ሥዩመ እግዚአብሔር፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በቤተ ሕዝቡ አፈ ጉባዔ፥ በቤተ ክህነቱ እጨጌና በቤተ ምልክናው ጸሓፌ ትእዛዝ የጋራ ስምምነት፡ የቀረበላቸውን የውሳኔ አሳብ አጽድቀው፡ በሰጡኝ ሢመት፡ ያበረከትኩት አገልግሎት ነው፡፡

በዚህ መሠረት፡ በቤተ ሕዝቡ፡ ከተራ የማኅበራዊ አገልግሎት ተሣታፊነት እንሥቶ፡ እስከአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት አባልነት፥ በብሔራዊ ሸንጎ የሕዝብ እንደራሴነትም፡ እስከሕግ መምሪያ ምክር ቤት አባልነትና እስከአኵስም ጽዮን ማኅበር ሊቀ መንበርነት፥ በቤተ ክህነቱ ደግሞ፡ ከዲቁና እንሥቶ፡ እስከቅስናና እስከደብር እልቅና፥ ከዚያም፡ እስከጠቅላይ ሥራ አስኪያጅነትና የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድነት፥ በቤተ ምልክናውም እንዲሁ፡ ከቋንቋ ተርጓሚነትና ልዩ ጸሓፊነት እስከክፍል ኃላፊነትና የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ድርጅት ሥራ መሪነት፥ ከዚያም፡ እስከብሔራዊው ሸንጎ፡ ሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባልነትና የአኵስም ጽዮን አውራጃ አስተዳዳሪነት፡ ተልእኮዬን ፈጽሜያለሁ፡፡ ከዚህ በቀር፡ ዋና ጽሕፈት ቤቱ፡ በስዊትዘርላንድ ዋና ከተማ፡ በጄኔቫ በኾነው፡ የዓለም ብሔራውያን የሕዝብ ሸንጎዎች ማኅበር፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሸንጎ ሙሴ (President of Inter- Parliamentary Union Ethiopian Group) በመኾን፡ ተግባሬን አከናውኛለሁ፡፡

## ለእግዚአብሔር ውለታ፥
## በግል የቀረበ፡ የምስጋና ሃሌታ!

ሃሌ ሉያ! አምላኬና መድኃኒቴ፥ ካህኔና ንጉሤ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ዘለዓለማዊው ክብርና ምስጋና የሚገባው፡ ለአንተና ለቅድስት እናትህ፡ ለድንግል ማርያም ብቻ ነው። ስለዚህ፡ እኔ፡ ከኹሉ ያነስሁት አገልጋያችሁ፡ ይህንኑ የሚገባችሁን ክብር ለመስጠትና ምስጋና ለማቅረብ የበቃሁ እኾን ዘንድ ፍቀድልኝ!

መላው ፍጥረተ ዓለም፡ በምልዓት ከተቀበለው ከመንፈስ ቅዱስ ጸጋህ፡ የኢትዮጵያዊነት ድርሻዬ የኾነችውን በረከት፡ እኔም እንድቀበል፡ ወሰን በሌለው፡ በመለኮታዊው ልግሥናህ ዐድለኸኛልና!


ይህችም በረከት፡ በቅዱሱ ኪዳንህ ስለተገለጸችው እውነትህ፡ በሕዝብና በአሕዛብ ፊት፡ እንዲህ በይፋ እመሰክር ዘንድ፥ መልእክትህንም፡ ወደሚመለከታቸው ኹሉ አደርስ ዘንድ፡ መንፈሳዊዉን ኃይልና ድፍረት ሰጥታኛለችና!


ከዚህ የተነሣ፡ በመለኮታዊው ቃልህ፡- *"በሰው ፊት፡ በእኔ አምኖ ለሚመሰክርልኝ ኹሉ፡ እኔ ደግሞ በሰማያት በአለው፡ አባቴ ፊት፡ ስለታማኝነቱ እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊት የሚክደኝንም፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት በአለው፡ በአባቴ ፊት፡ ስለክህደቱ እመሰክርበታለሁ።"* ስትል ያሰማኸው፡ ዘለዓለማዊው የጥሪ አዋጅህ፡ በእኔ፡ በትሑቱ አገልጋይህ[፺፪] ዘንድ ተደማጭነትን አግኝቶ፡ ተፈጽሟልና! ለዘላለሙ አሜን።

\+ + + + + + +

የዓለሙ መፋረጃ!


# ክፍል ኹለት






ኪዳነ ሙሴ፡ (ሓተታው፡ በገጽ ፸፫-፩፻፬ ይገኛል።)

ኢትዮጵያ፡





ኪዳነ ሙሴ፤ (ሐተታው፡ በገጽ ፸፭-፩፻፬ ይገኛል።)



በእግ
ላይ፡ በ

በቅ
መ

አስደ

ኢትዮጵያ፡



ኪዳነ ምሕረት።
(ሓተታው፡ በገጽ ፩፻፲፭-፩፻፲፮ እና ፩፻፶፬-፩፻፶፰ ይገኛል።)



October 31, 1996

Ermias Kebede
Ethiopia: The
P.O. Box 43262
Washington, D.C

Greetings Nib

I greet you in
to us, the Rasta
kings, Conque

Your letter
contents have
documented
of Ethiopia in

However, Rast
Selassie the
and the entire
and divinity.


*"Juda*
*Thy*
*Thy*

In 1930, Nov
coronation
read and ch

*"Give*
*and T*

His Majesty
the anointing
*Judah"*, fulf
*from betwee*
The sword,
imperial ve

የዓለሙ መፋረጃ!



ከምስተር ካርል ፊልፖትስ ናፍታሊ የተጻፈው
ደብዳቤ:- በእንግሊዝኛ

October 31, 1996

Ermias Kebede Wolde-Yesus, Nibure-Id
Ethiopia: The Kingdom of God Services
P.O. Box 43262
Washington, D.C. 20010-9262

Greetings Nibure-Id:

I greet you in the precious name of Our Lord and Saviour, Jesus Christ, who has revealed himself to us, the Rastafarians, through the personality of H.I.M. Emperor Haile Selassie the 1st. King of kings, Conquering Lion of the Tribe of Judah, Elect of God, Light of this world, King of Zion.

Your letter and manuscript dated, May 24, 1996 was received. Thanks for the translation. The contents have been well read and considered. Ethiopia's role in history and the Bible was well documented and elaborated upon. It confirms our life struggle, that is, to maintain the integrity of Ethiopia in these desolate places.

However, Rastafarians will never fail to give thanks and praises for H.I.M. Emperor Haile Selassie the 1st. We are witnesses to what he has been to us, done for us, for Ethiopia, Africa and the entire world! We therefore stand before you and all mankind to testify of His integrity and divinity. As it is written in Genesis 48 v. 8, concerning the blessing of Judah:

> *"Judah, thou are he whom thy bretheren shall praise;*
> *Thy hand shall be in the neck of Thine enemies;*
> *Thy father's children shall bow down before thee."*

In 1930, November the 2nd, the people of Ethiopia through their church, administered the coronation of Ras Tafari to the Throne of Solomon. At this coronation, the 72nd Psalms was read and chanted by priests continuously:

> *"Give the King Thy judgements, Oh God,*
> *and Thy righteousness to the King's Son."*

His Majesty was invested with the seven symbols of divine Kingship. The crown, symbolizing the anointing by God as earth's rightful Ruler; the sceptre enscribed *"the Lion of the Tribe of Judah"*, fulfilling Genesis 49 v. 10: *"The sceptre shall not depart from Judah, nor a lawgiver from between his feet, until Shiloh come; and unto him shall the gathering of the people be."* The sword, the golden globe of the earth, two lances, the diamond encrusted ring, and the imperial vestments, were all given to Him.

Now there is one question that I would like to ask; the crowning of His Majesty as King of kings, Lion of Judah, Elect of God, Light of this world; was this anointing of men or of God -- was it from Heaven or the will of men?

In asking all this, we are aware that the Throne of Ethiopia is God's Throne. However, He has forever chosen the seed of David and Solomon to represent Him to mankind until He whose right it is comes [Shiloh]. So would not all the kings who sit on God's earthly Throne, wear His titles, being His representatives? Why should it then offend you, for His Majesty, Haile Selassie the 1st to be called *"The Lion of the Tribe of Judah?"* There must be one to represent Him as long as the sun and moon are in the sky.

As the Ethiopian constitution of 1954, clearly stated: *"By virture of the anointing that He has received and by virtue of Royal blood, the person of His Majesty is sacred. Anyone be so bold as to touch the person of His Majesty will be severly punished."* The scriptures also says: *"Touch not the Lord's anointed, nor do his prophet any harm."*

Now Nibrue-Id, your article was going quite well, until you became so bold as to touch the person, character and integrity of His Imperial Majesty, the Lord's anointed. I consider it as *"touching"* when one attacks the integrity, or attempts to tarnish another's character and memory. As His Majesty has said in His autobiography: *"Some people have written the story of My life, representing as truth what in fact derives from ignorance, error or envy; but they cannot shake the truth from its' place, even if they attempt to make others believe it."* [My Life and Ethiopia's Progress]

On page 56 of your article, in the second paragraph, you wrote: "Atse Menelik's complete faith and full reliance on the Holy Covenant brought about the astounding victory over the powerful Italian invading army. On the contrary, Atse Haile Sellassie's denial and defilement of the Holy Covenant by his adherence to and trust in the covenant of the League of Nations entailed his defeat by the Fascist Italian army of Mussolini, the Catholic." This defeats your claim to be presenting "divine truth" to Ethiopians and the rest of the world.

I must mention here before proceeding, that one should not confuse the seven covenants of the Holy Bible with the covenant of the League of Nations. A covenant is an agreement, a promise entered into by two or more parties. The covenants of God were His promises to His people throughout the ages. The covenant of the League was a promise or agreement entered into among men. His Majesty believed in God's covenants and He is a living testimony of it [Davidic Covenant].

Any student of history, will attest to the wisdom and statesmanship of H.I.M. in winning Ethiopian, a black nation, into the membership of the League of Nations, *at a time* when all peoples of color were under colonial rule. This was a convenant amongst free nations to uphold a sacred principle, known as "collective security." This principle states that all members are bound to defend each other against agression to its' territorial integrity and sovereignty. This principle of defending the weak against the agression and evil of the strong through collective

action of the lovers of freedom, is one of the noblest and most sacred principles of the family of nations. In fact, it is upon this principle that the peace and security of all nation's rests.

By leading Ethiopia into membership of the League, His Majesty was challenging the collective conscious of mankind to uphold a principle, that if implemented, would safeguard the independence of Ethiopia, and the future independence of all peoples. His Majesty knew that Europe's scramble for Africa had reached the gates of Ethiopia. The responsibility for Ethiopia's independence now rested also on the shoulders of all signatures to the League.

Now is it because His Majesty believed in this principle why Ethiopia was invaded, and His Majesty exiled? Of course not! But rather the failure of men to live up to this covenant. The hypocracy, racism, envy, deceitfulness and selfishness of some of the members of the League resulted in the League's failure to support Ethiopia, one of its' members, against agression.

As His Majesty told them: "God and history will remember your judgement.... It is not only Ethiopia's independence which is at stake, but the very existence of the League.... It is international morality which is at stake.... Today it is us, tomorrow it will be you."

Did not the world enter into its bloodiest judgement for allowing Rome to violate Ethiopia? Wasn't World War II a direct result of the League's failure to live up to its covenant with Ethiopia? Did not the Almighty take His Majesty through the flames of a burning Europe and restore Him back to His Throne 5 years later?


So how can you blame His Majesty for believing in a noble principle by saying it is this belief that that caused the defeat of Ethiopia? Are you God to judge His anointed? Is it not clear that until Ethiopians acknowledge and confess the good and blessings they received under the leadership of H.I.M. Emperor Haile Selassie the 1st, and hearken unto His words of wisdom, they, as a rebellous people, will dwell in a dry land.

Long Live Haile Selassie the 1st! Psalms 72 verse 17: *"His name shall endure forever: His name shall be continued as long as the sun: and men shall call Him blessed: all nations shall call him blessed."*

God Save the King!

Karl Phillpotts

Karl Phillpotts Naphtali



አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር፡
ማይጨው ላይ ድል ከኾኑ በኋላ፡ ወደጄኔቫ ኼደው፡
ኢትዮጵያ፡ አባል ተደርጋበት ለነበረው፡ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔ፡
አቤቱታቸውን ሲያሰሙ፤ (ሓተታው፡ በገጽ ፫፻፷፬-፫፻፸፯ ይገኛል።)



(ከላይ ከሠ

አክቶበር 31, 19

ኤርምያስ ከበደ
ኢትዮጵያ፡ የእ
መልእክት ሣጥን
ዋሽንግተን፥ ዲ


ሰላም! ንቡረ እ

ለእኛ ለራስተ
(ከይሁዳ ነገድ
የዚህ ዓለም
ቀዳማዊ ኃይ
መድኃኒታችን
እልዎታለሁ።
በሚይ
ደርሷል።
ያስመሰግናል።
ኢትዮጵያ፡
ሰነዶች ተደ
ኹለንተናዊ
ጠብቀን ለ
ይኹ
ኃይለ ሥላሴ
እርሳቸው፡
ለኢትዮጵያ፥
ስለዚህ፡
አምላክነታቸ
በመላው የሰ
ዘፍጥረት ም

(በ19
አማካይነት፡
ዙፋን ላይ
(እንግሊዝኛ



አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር፡
ማይጨው ላይ ድል ከኾኑ በኋላ፡ ወደጄኔቫ ኼደው፡
ኢትዮጵያ፡ አባል ተደርጋበት ለነበረው፡ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔ፡
አቤቱታቸውን ሲያሰሙ፡ (ሐተታው፡ በገጽ ፫፻፸፬-፫፻፹፯ ይገኛል።)



አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. በፋሺስት ጣልያን ጦር፡
ማይጨው ላይ ድል ከኾኑ በኋላ፡ ወደጄኔቫ ኼደው፡
ኢትዮጵያ፡ አባል ተደርጋበት ለነበረው፡ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔ፡
አቤቱታቸውን ሲያሰሙ፤ (ሓተታው፡ በገጽ ፫፻፷፬-፫፻፹፮ ይገኛል።)

በዚህም ሥርዓተ ንግሥ ላይ፡ ካህናቱ፡ ከዳዊት መዝሙራት፡-

*“አቤቱ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ!*
*ጽድቅህንም፡ ለንጉሥ ልጅ!”*

የሚለውን፡ 72 (፸፪)ኛውን መዝሙር ደግመውታል፤ ወረቡንም፡ በዜማ እየመላለሱ አሸብሽበውታል።

በዚሁ ሥርዓት ላይ፡ የመለኮታዊው ንጉሥነት ማረጋገጫ የኾኑትን ሰባቱን ምልክቶች እጅ አድርገዋል። እነዚህም፡ በምድር ላይ፡ በእግዚአብሔር ተቀብተው፡ የዚች ዓለም ሕጋዊ ገዢ መኾናቸው የሚታወቅበትን ዘውድ፥ በኦሪት ዘፍጥረት፡ ምዕ. ፵፱፥ ቊ. ፲፡ *“በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም፤ የገዢም ዘንግ፡ ከእግሮቹ መካከል፤ ገዢ የኾነው እስኪመጣ ድረስ፥ የአሕዛብ መታዘዝም ለእርሱ ይኾናል”* ያለው የተፈጸመ መኾኑን በማስታወቅ፡ *“ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ”* የሚለው ቃል የተቀረጸበት በትረ መንግሥት፥ ሠይፍ፥ የዓለም ምሳሌ የኾነው ከወርቅ የተሠራው ሉል፥ ኹለቱ ጦሮች፥ በዕንቊ ፈርጥ ያጌጠው ቀለበትና ልብሰ መንግሥቱ ሲኾኑ፡ እነኚህ ኹሉ፡ ለእርሳቸው ይኾኑ ዘንድ ተሰጥተዋቸዋል።

እዚህ ላይ፡ ላቀርብ የምፈልገው፡ አንድ ጥያቄ አለኝ፤ ይኸውም፡ “ግርማዊ ጃንሆይ፡ የንጉሦች ንጉሥ፥ የይሁዳ አንበሳ፥ ሥዩመ እግዚአብሔር፥ የዓለም ብርሃን ኾነው ዘውዱን የተቀዳጁ ከኾኑ፡ ይህ ቅብዓት፡ የሰዎች ነበርን? ወይስ የእግዚአብሔር? ከሰማይ ነበርን? ወይስ ከሰዎች ፈቃድ የተገኘ?” የሚል ነው።

ይህን ጥያቄ ስናቀርብ፡ የኢትዮጵያ ዙፋን፡ የእግዚአብሔር ዙፋን መኾኑን ተገንዝበን ነው። ይኹንና፡ ገዢ የኾነው እስኪመጣ ድረስ፡ በሰው ትውልድ ዘንድ እርሱን ይወክል ዘንድ፡ የዳዊትንና የሰሎሞንን ዘር፡ ለዘለዓለም መርጧል። ስለዚህ፡ በእግዚአብሔር ምድራዊ ዙፋን ላይ የሚቀመጡት ነገሥታት ኹሉ፡ ወኪሎቹ እንደመኾናቸው መጠን፡ የማዕርጋቱን ስሞች ሊቀዳጁ አይገባምን? ታዲያ፡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፡ “ከይሁዳ ነገድ የተገኘው አንበሳ” ተብለው ቢጠሩ፡ እርስዎን፡ ለምን እንዲህ የሚያስቀይምዎ ኾነ? መቼም፡ ፀሓይና ጨረቃ በሰማይ ላይ እያበሩ እስካሉ ድረስ፡ እርሱን የሚወክል አንድ ሰው መኖር አለበት።

በ፲፱፻፹፯ ዓ. ም. በወጣው፡ የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ውስጥ፡ በግልጽ እንደተጻፈው፡ *“የግርማዊነታቸው ሰውነት፡ ቅብዓ መንግሥትን በመቀባቱና ከንጉሣዊው ዘር በመወለዱ፡ የተቀደሰ ነው፤ ከዚህ የተነሣ፡ በግርማዊነታቸው ሰውነት ላይ እጁን ለማንሣት የደፈረ፡ ማናቸውም ሰው፡ በጽኑ ይቀጣል።”* እንዲሁም፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል፡ *“እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ! በነቢዩም ላይ ምንም ዓይነት ጉዳትን አታድርስ!”* ይላል።

እንግዴህ፡ ንቡረ እድ ሆይ! እግዚአብሔር በቀባው፡ በግርማዊነታቸው ሰውነት፥ ጠባይና ኹለንተናዊነት ላይ እጅዎን ለማንሣት እስከደፈሩበት ሥፍራ ድረስ፡ ጽሑፍዎ፡ በጥሩ ይዘት ሲቀጥል ቆይቶ ነበር። አንድ ሰው፡ የሌላውን ኹለንተናዊነት ሊያጠቃ ከተነሣ፥ ወይም፡ የሌላውን ጠባይና መታሰቢያ ሊያጎድፍ ከሞከረ፡ እኔ፡ ይህን አድራጎት፡ በሌላው ላይ፡ እንደ *“እጅ ማንሣት”* እቆጥረዋለሁ።

## የዓለሙ መፋረጃ!

ግርማዊ ጃንሆይ፡ [ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ] ብለው፡ ራሳቸው በጻፉት የሕይወት ታሪካቸው ውስጥ፡ "አንዳንድ ሰዎች፡ ካለማወቅ፥ ከመሳሳትና ከምቀኝነት የተነሣ፡ እውነት እያስመሰሉ፡ ስለእኔ የሕይወት ታሪክ ጽፈዋል። ነገር ግን፡ ምንም እንኳ፡ ሌሎችን ለማሳመን ቢሞክሩም፡ እውነትን ከቦታዋ ሊያነዋውጿት ከቶ አይችሉም" እንዳሉት ማለት ነው።

በጽሑፍዎ ገጽ ፶፮፥ በ፪ኛው አንቀጽ፡ እንዲህ የሚል ቃል አሥፍረዋል፡- "አጼ ምኒልክ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ፍጹም እምነትና ሙሉ ትምክህት ስለነበራቸው፡ እነሆ፡ ያን፡ ኃያል የነበረውን፡ የጣልያን ወራሪ ጦር፡ እጅግ በሚያስገርም ኹኔታ ድል አደረጉት። በዚህ አንጻር ደግሞ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በዠኔቭ በነበረው፡ የመንግሥታት ማኅበር ላይ፡ ፍጹም እምነትን በመጣል፡ በዚያ ቃል ኪዳን በመማጸናቸውና በእርሱ ብቻ በመታመናቸው፡ ይህ አድራጎት፡ ቅዱሱን ኪዳን እንደመካድና እርሱን እንደማርከስ ስላስቆጠራቸው፡ እነሆ፡ በካቶሊካዊው ሙሶሎኒ በሚመራው፡ የጣልያን ፋሺስታዊ ጦር ሠራዊት የመሸነፍ ውርደትን አስከተለባቸው።"

ይህ ቃል፡ "የእግዚአብሔርን እውነት" ለኢትዮጵያውያንና ለቀረው የዓለም ሕዝብ የማድረስ ግዳጅ አለብኝ የሚለውን አቋምዎን፡ ውድቅ ያደርገዋል።

ጽሑፌን ወደፊት ከመቀጠሌ በፊት፡ እዚህ ላይ ላወሳው የሚገባኝ፡ አንድ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተመዘገቡትን ሰባቱን ቃል ኪዳናትና የመንግሥታት ማኅበርን ቃል ኪዳን እንዳናመሳስላቸው ነው። ቃል ኪዳን፡ በኹለት ወይም ቁጥራቸው ከዚያ በላይ በኾኑ ወገኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት፥ ወይም የሚሰጥ የተስፋ ቃል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳናት፡ እርሱ፡ በየዘመናቱ፡ ለሕዝቡ የሰጣቸው የተስፋ ቃላት ነበሩ። የመንግሥታቱ ማኅበር ቃል ኪዳን፡ ሰዎች በመካከላቸው የተሰጣጡት የተስፋ ቃል፡ ወይም የተዋዋሉት ስምምነት ነበር። ግርማዊ ጃንሆይ፡ በእግዚአብሔር ቃል ኪዳናት ያምኑ ነበር፤ ለእርሱ [ለዳዊት ቃል ኪዳን]፡ ሕያው ምስክር ናቸው።

ነጭ ያልኾኑ ሕዝቦች ኹሉ፡ በቅኝ አገዛዝ ቀምበር ሥር ወድቀው በነበሩበት ዘመን፡ አንዲት ጥቁር አገር፡ ኢትዮጵያን፡ የመንግሥታት ማኅበር አባል ለመኾን እንድትችል ማብቃት፡ የግርማዊነታቸውን ብልህነትና መንግሥታዊ አመራር ፈሊጠኛነት የሚያረጋግጥ መኾኑን፡ ማንኛውም የታሪክ ተማሪ ይመሰክራል። ነጻ አገሮች፡ "የጋራ ፀጥታ ጥበቃ" የተባለውን የተቀደሰ መሠረታዊ አሳብ፡ በመካከላቸው አጽንተው ለማቆየት፡ የተጋቡት ቃል ኪዳን ይህ ነበር። አባሎች ኹሉ፡ የየግዛታቸውን ኹለንተናዊነትና ሉዓላዊነት፡ እርስ በርሳቸው በመረዳዳት፡ ከወራሪ ጥቃት ተከላክለው ለማዳን የሚችሉበትን ዘዴ፡ ይህ መሠረታዊ አሳብ ይገልጻል። በነጻነት አፍቃሪዎች የጋራ ተግባራዊ ድጋፍ፡ ደካማውን፡ ከኃያሉ ወራሪ ጥቃትና ግፍ ተከላክሎ ማዳንን የሚያጸድቀው ይህ መሠረታዊ አሳብ፡ የዓለም ኅብረተሰብ ከሚከተሏቸው፡ እጅግ ከተከበሩትና ከተቀደሱት መሠረታውያን አሳቦች መካከል አንዱ ኾኖ ይገኛል። በእርግጥም፡ የአህጉራት ኹሉ ሰላምና ደህንነት ጸንቶ ያለው፡ በዚህ መሠረታዊ አሳብ ላይ ነው። የግርማዊነታቸው፡ ኢትዮጵያን፡ ለዚህ የመንግሥታት ማኅበር አባልነት ማብቃት፡ ለመላው የሰው ዘር፡ የጋራ ሕሊና የቀረበ ፈተና ነበር።

ይኸውም: በተግባር ላይ የዋለ እንደኾነ: የኢትዮጵያን ነጻነትና የሌሎቹን ሕዝቦች ኹሉ: የወደፊት ነጻነት ሊጠብቅ የሚያስችለው: ይህ መሠረታዊ አሳብ: ይከበር ወይም አይከበር እንደኾነ የሚታይበት በመኾኑ ነው:: ኤውሮጳ: በአፍሪቃ ላይ የተያያዘው መቀራመት: ከኢትዮጵያ ደጃፍ መድረሱን: ግርማዊነታቸው አውቀታል:: በዚህ ጊዜ: የኢትዮጵያን ነጻነት የማስከበሩ ኃላፊነት: በመንግሥታቱም ማኅበር የቃል ኪዳን ተዋዋዮች ኹሉ ላይ የወደቀ ኾነ!

ታዲያ÷ ኢትዮጵያ የተወረረችው÷ ግርማዊነታቸውም የተሰደደው: ግርማዊነታቸው: በዚህ መሠረታዊ አሳብ ስላመነበት ነውን? በፍጹም አይደለም! ነገር ግን: ሰዎች: ለዚህ: ለገቡበት ቃል ኪዳን ራሳቸውን ባለማብቃታቸው ነው እንጂ:: በአንዳንዶቹ: የመንግሥታቱ ማኅበር አባሎች ዘንድ ከነበረው ግብዝነት÷ ዘረኛነት÷ ምቀኛነት÷ ሸንጋይነትና ራስወዳድነት የተነሣ: ከአባሎቹ መካከል: አንዲቱ የኾነችውን ኢትዮጵያን: ከወረራ ለማዳን የሚያስችለውን ድጋፍ ለመስጠት: የመንግሥታቱ ማኅበር ተሣነው::

ይህንኑም: "እግዚአብሔርና ታሪክ የምትሰጡትን ፍርድ: ሲያስታውሱት ይኖራሉ:: ...በአሥጊ ኹኔታ ላይ የሚገኘው: የኢትዮጵያ ነጻነት ብቻ ሳይኾን: የራሱም: የመንግሥታቱ ማኅበር መሠረታዊ ህልውና ጭምር ነው፤ ...በመንግሥታት መካከል ሊጠበቅ የሚገባው መልካም የሥነ ምግባር ግንኙነት: በአሥጊ ኹኔታ ላይ ይገኛል::...ዛሬ ለእኛ የኾነው ይህ ጽዋ: ለነገ የሚጠብቃችሁ ደግሞ: እናንተን ነው::" ሲል: ግርማዊነታቸው ለእነርሱ ተናግሮታል::

ሮማ: የኢትዮጵያን መብት እንድትደፍር: ዓለም በመፍቀዱ: በራሱ ላይ እልቂትን ያስከተለ ፍርድን አልተቀበለምን? ኹለተኛው የዓለም ጦርነት: የመንግሥታቱ ማኅበር: ለኢትዮጵያ የገባውን ቃል ኪዳን ባለማክበሩ የደረሰበት የግብሩ ውጤት አይደለምን? ኃያሉ አምላክ: ግርማዊነታቸውን: በኤውሮጳ በነደደው: የእሳት ነበልባል ውስጥ አሳልፎ: ከአምስት ዓመታት በኋላ: ወደዙፋናቸው አልመለሳቸውምን?

ታዲያ÷ [ማይጨው ላይ በጣልያን ጦር] የኢትዮጵያን መሸነፍ ያስከተለው ይህ እምነት ነው በማለት: ግርማዊነታቸው: ክቡር በኾነ መሠረታዊ አሳብ በማመኑ: እንዴት እርስዎ ሊወቅሱት ይችላሉ? እርሱ በቀባው ላይ: ዳኝነት ለመስጠት: እርስዎ እግዚአብሔር ነዎትን? ኢትዮጵያውያን: በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አመራር: ያገኙትን መልካም ነገርና የወረደላቸውን በረከት አውቀው: በእምነት እስካልተቀበሉና እስካልመሰከሩ ድረስ÷ የተናገሩዋቸውንም የጥበብ ቃላት ሰምተው እስካልፈጸሙ ድረስ: እንደዐመፀኛ ሕዝብ ተቆጥረው: መኖሪያቸው ምድረ በዳ ኾኖ እንደሚቀር: ግልጽ አይደለምን?

ረዥም ዕድሜ: ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ! መዝሙር: ፸፩ (፸፪) ቁጥር ፲፯:- *"ስሙ ለዘለዓለም ቡሩክ ይኾናል! ከፀሓይም አስቀድሞ ስሙ ይኖራል! የምድር አሕዛብ ኹሉ በእርሱ ይባረካሉ! አሕዛብ ኹሉ ያመሰግኑታል::"*

እግዚአብሔር ንጉሡን ይጠብቅ!

(ጽሑፍ ኪዳን)

ካርል ፊልፖትስ ናፍታሊ



December 30,

እነዚህም: የሚከተሉት ናቸው:-

፩ኛ:- ገና በመጀመሪያ: እርስዎ: ወደእኔ መጥተው በተዋወቅንበት ዕለት: ስለኢትዮጵያና ስለተቀደሱት ውርሶቿ: ከእኔ ለመማርና ለማወቅ: በእውነት ፈልገው የቀረቡኝ መስሎኝ ነበር:: ይልቁንም: በእኔ መኖርያ ቤት ካደረግነው: ከዚያ ትውውቃችንና ውይይታችን በኋላ፥ ተከታትሎም: በባልቲሞር ከተማ በሚገኘው: *ሬዲዮ ዋን* በተባለው የነፋስ ድምፅ መነጋገሪያ ትርኢት ጊዜ: ካካኼድነው የቃለ መጠይቅ ምልልስ በኋላ: በእርግጥ በልቤ: አሳድሬው የነበረው ተስፋ: "እንግዴህ: የእግዚአብሔር ወደኾነው: ወደመልካሙ ግብ: ይደርሳሉ!" በሚለው እምነቴ ላይ የተመሠረተ ነበር::

ይኸውም: ከእኔ: በጥራዝ መልክ ታትሞ የተላከልዎትን ጽሑፍ በሚያገኙበት ጊዜ: የጽሑፉ መልእክት: ስለኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት ከምታስታውቅዎት: ከዚያች: ከእግዚአብሔር እውነት ለመድረስ የሚያደርጉትን ፍለጋ: ወደፍጻሜው ብቅዓት ከፍ ለማድረግና በዚህ ረገድ ያገኙትን እውቀትዎን በበለጠ ለማጠናከር ያግዝዎታል የሚለው እምነቴ ነው:: ነገር ግን: እንዲህ ሳይኾን ቀርቶ: እንዲያውም ይግረምህ፥ ያሳዝንህም ብሎ: ያላሰብሁትን ምላሽ የያዘው ደብዳቤዎ ደረሰኝ::

ይህ ኹሉ: ከላይ የተገለጸው የመገናኛው፣ና የመተዋወቂያው፥ የመነጋገሪያውና በይፋ የማስተማሪያው ዝግጅት የተወጠነው፥ የተከናወነውም: በሕመም ምክንያት: ለረዥም ጊዜ: በቤት ተወስነው የቆዩት: የቀድሞው ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ባለቤት በኾኑት: በልዕልት መድፈሪያሽ ወርቅ አበበ አማካይነት እንደነበረ: እርስዎ ራስዎም: ደህና አድርገው ያስታውሱታል:: [ልዑል አልጋ ወራሽ ገና በሕይወት እያሉ: ለእርስዎ ደብዳቤ መልስ ኾኖ የተሰጠዎት ይህ ጽሑፍና ከእርሱ በፊት የተላለፈው መልእክት: የኹለቱንም ቅጂዎች ልኬላቸው: የደረሳቸው መኾኑን: ልዕልት አረጋግጠውልኛል::]

፪ኛ:- በመጀመሪያው ጽሑፌ: በተለይም: በመቅድሙ ውስጥ ተብራርቶ የተገለጸውን: የመለኮታዊዉን መልእክት ዓቢይ ዓላማ: በትክክል እንደተገነዘቡት ተስፋ አደርጋለሁ:: በአጠቃላዩ ትግል: ሊደረስባቸው ከታቀዱት ግቦች መካከል አንዱ: የእግዚአብሔር ከኾነችው እውነት: ወጥተው: በስሕተቱ ምድረ በዳ የሚባዝኑትን ለመመለስ ሲኾን: በኃያሉ አምላክ እርዳታና አመራር: የዚችን እውነት ትክክለኛ ገጽታ: ካልተበከለው የኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ አኳያ በመመልከት፥ በገሃድ በማቅረብና በቅን በማስተላለፍ: ይህን ግዳጅ: ለፍሬ ለማብቃት: የተቻለኝን ኹሉ ሳልቆጥብ አድርጌአለሁ::

፫ኛ:- የመልእክተኛ ተግባሩ: የተልእኮ ግዳጁን መፈጸም፥ ያም: መልእክቱን ማድረስ መኾኑን: ማነኛውም ሰው የሚያውቀው ተራ ነገር ነው:: መልእክቱን መቀበልና መፈጸም፥ ወይም "አልቀበልም" ብሎ መመለስ ወይም ተቀብሎ ቸል ማለት ደግሞ: የተላከለት ተቀባይ መብትና ኃላፊነት ነው:: እንግዴህ: እርስዎም: "*የእግዚአብሔር እውነት: ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት ምን ትላለች?*" የሚለው መልእክት: ከደረሳቸው ተጠያቂዎች መካከል: አንዱ ስለኾኑ: መልእክቴን በማድረስ: ለዘመኑ ተገቢነት ያለውንና እስካሁን መሰል የሌለውን: ይህን ተልእኮዬን መፈጸሜን: በምስክርነት ያረጋግጣሉ::

ወይስ፡ በአጼ ኃይለ ሥላሴና እንዲሁም፡ በዘመናቸው፡ በእርሳቸው ሥር፡ የሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት የአገልግሎት ቤቶች፡ ማለትም፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው ተጠሪዎች በኾኑት ባለመንበሮች አማካይነት፡ በግል ሰውነቴ የተቀበልኳቸውን ሥልጣናት፡ እርስዎ፡ እንደሌሉ መቁጠርዎ ነውን? እንዲህ እንዳይባል ደግሞ፡ እርስዎ ራስዎም፡ በዚያ የነፋስ ድምፅ፡ የንግግር ትርኢት ላይ፡ በአንደበትዎ በተናገሩዋቸው የማስተዋወቂያ ቃላት፡ በሕዝብ ፊት፡ በይፋ፡ እውቅና የሰጧቸው መስለው ታይተዋል። ታዲያ፥ በዚህ በአሁኑ ኹኔታዎ፡ እርስዎ ያሳዩት ይህ የአስተያየት ለውጥ፡ በእርስዎ ዘንድ፡ ኾነ ተብሎ፡ ታስቦበት፥ ወይም በዕቅድ ተዘጋጅቶ የተፈጸመ ድርጊት ነውን? ወይስ፡ ከዚህ የተለየ፡ ሌላ መነሻ ምክንያት አለዎት?

ስለእኔ ያለዎት፡ የሕሊና አስተያየት፡ ለምን እንደተቀየረ፥ የነበረዎትም የአክብሮት ስሜት ተለውጦ፡ ለምን በተቃራኒው እንደተተካ፡ ከዚህ ከያዝነው ጉዳይ በመነሣት፡ የግምት አሳቤን እንድሰጥ ቢፈቅዱልኝ፡ ለዚህ ኹሉ ምክንያቱ፡ በቀላሉ፡ "*የእግዚአብሔር እውነት፡* አጼ ኃይለ ሥላሴን በሚመለከት፡ የምትለው ይህ ነው" ብዬ፡ በጽሑፍ በመግለጤ፡ "እጅግ ተዳፈረ" ብለው በማሰብዎ ይመስለኛል።

እንግዲህ፡ ነገሩ ይህ ከኾነ፥ እርስዎም፡ ባሁኑ ጊዜ፡ ስለእኔ ትክክለኛውን እውቀት፡ በሚበቃ እንዳገኙ በማመን፡ ስለዘመኑ መጨረሻ፡ በትንቢት የተነገረው ቃል በሚፈጸምበት፡ በዚህ አሳሳቢ ጊዜ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለመኾኗና እርሷም፡ ለብዙ ሺህ ዓመታት፡ በታማኝነት ጠብቃ ስላቆየችው ስለቅዱሱ ኪዳን የምትናገረውን የእግዝአብሔርን እውነት በማገልገል፡ የምድር ወይም የጠፈር፥ የሰው ወይም የመላእክት፥ የእርስዎ ወይም የእኔ ከሚባሉት፡ ከሌሎቹ ኹሉ አስመሳይ እውነቶች፡ ተለይታና ልቃ፡ ምልዕት በኾለሄ ስለኾነችው፡ ስለዚችው፡ *የእግዚአብሔር እውነት፡* ትምህርታዊ ቃሉን፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በማይበገር ድፍረት ለማሰማት፡ ግዳጅ ኖሮበት የሚቀርብ፡ ሌላ ማን ይመጣል ብለው ይጠብቃሉ?


፯ኛ:- በእርስዎ ሕሊና፡ ይህን ያህል ሁከት ፈጥሮ፡ ያን በመሰለ መልክ፡ በጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ ያነሣሣዎ ምክንያት፡ ቀደም ብሎ፡ በእኔ አማካይነት በደረሰዎት የጽሑፍ መልእክት ውስጥ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ ለቅዱሱ ኪዳን የገቡትን ውለታ አክብረው ስላለመፈጸማቸው የምትናገር፡ አንዲት ንዑስ ዐረፍተ ነገር፡ "ለምን ተጻፈች?" በማለት መኾኑን፡ ራስዎ፡ በደብዳቤዎ ካመለከቱት ጋር፡ ከዚህ በሚቀጥሉት ገጾችም ተብራርቶ ይነበባል። ታዲያ፥ ይህች ንዑስ ዐረፍተ ነገር ከገለጸችው ይልቅ፡ የባሱ፡ እጅግ ግልጽና ጽኑ የኾኑ፡ መራራ ክሥተቶችን የያዙ፡ ሌሎች ዐረፍተ ነገሮች፡ *የእግዚአብሔር እውነት* መልእክተኛ በኾነው፡ በዚህ በኹለተኛው ጽሑፍ ውስጥ በብዛት ሠፍረው ሲያገኟቸው፡ እንዴት ሊኾኑ ነው? ኹኔታውንስ፡ እንዴት ይቋቋሙታል?

በዚህም፡ *"የእግዚአብሔር ድምፅ፡ የእሳቱን ነበልባል ይቆርጣል! የእግዚአብሔር ድምፅ፡ ምድረ በዳውን ያናውጣል!"*[፲፱] የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል መፈጸሙ አይደለምን?

የዓለሙ መፋረጃ!

፲ኛ:- እንግዴህ: ምንም እንኳ: ደብዳቤዎ: በአሉታና በተቃርኖ መልሶች የተመላ ኾኖ ባገኘውም: እኒህ: በእርስዎና በእኔ መካከል የተነሡት አከራካሪ ጉዳዮች: በመልካም መግባባት እንዲፈቱ ለማድረግ: ችሎታው በማይወሰነው: በመንፈስ ቅዱስ አመራር ላይ ባለኝ ሙሉ እምነት ጸንቼ: ተስፋ ሳልቆርጥና ወደኋላ ሳልል: የበኩሌን ድርሻ በማበርከት: የመልእክተኛነት ተግባሬን ለመቀጠል: ይኸው ጨክኜ ወስኜ ተነሥቻለሁ::

ስለዚህ: እርስዎም: አስተሳሰብዎን ወደበጎው አቋም በማቃናት: እስካሁን የተገለጹትን ቁምነገሮች ኹሉ: እንደገና እንዲያመዛዝኗቸውና ከዚህ ቀጥሎ: በተጨማሪ ሓተታ ተብራርታ ከቀረበችው: ከመጨረሻዋ እውነት፥ እርሷም: የእግዚአብሔር ከኾነችው እውነት ለመድረስ የጀመሩትን ፍለጋ: በታማኝነት ይቀጥሉ ዘንድ: እውነተኛነትዎን በመፈታተን: አደፋፍርዎታለሁ::



ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ ሞቻል)::
(ዝክረ ነገራቸው: በገጽ ፩፻፷፭-፷፱ ይገኛል::)

# ምዕራፍ ፩

## የፍሬ ጉዳዩ፡ መሠረታውያን መንሥዔዎች።

ከላይ የተገለጸው ሐተታ፡ ለዚህ፡ ለኹለተኛው የመጽሓፍ ክፍል፡ መቅድም ኾኖ ያገለግል ዘንድ፡ በቂ እንደሚኾን በማመን፡ ከእርሱ ቀደም ብሎ በተጠቀሰው ደብዳቤዎ ውስጥ ለተወሳው ዓቢይ ጉዳይ፡ መሠረታውያን መንሥዔዎች የኾኑትን ነገሮች፡ እንደሚከተለው፡ አንድ በአንድ መተንተን እጀምራለሁ።

እኛ፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በእግዚአብሔር ላይ ካለን ጽኑ እምነት የተነሣ፡ ራሳችንን፡ ለእርሱ ለፈጣሪያቸን፡ በፍጹም እንድናስገዛና በማያወላውል እንድንታዘዘው ይጠበቅብናል። አንገተ ደንዳናነትና የእብሪት እልኸኝነት፡ በትውፊት ከእኛ የደረሰውን መንፈሳዊ ዝንባሌያችንንና ሃይማኖታዊ ትሕትናችንን ሊያጠቃው ሲሞክር፡ ዝም አንልም። ሰዎች፡ በታሪካቸው፡ በተለይም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን እንደነበሩት፡ እንደአይሁድ ያሉ የሃይማኖት አክራሪዎች፡ በአስተሳሰባቸውና በአድራጎታቸው፡ ጉልህ አድርገው ያሳዩትን የመሰለውን፡ አንጎተ ደንዳናነትና የእብሪት እልኸኝነት ማለት ነው።

### ኢትዮጵያ፡<br>"ራስ ተፈሪያውያን"ን<br>በእግዚአብሔር እውነት ስትፋረድ!

እውነትን፥ እርሷም የእግዚአብሔር የኾነችውን እውነት፡ ማነኛችንም፡ ከየራሳችን ልናፈልቃት፥ ወይም ያፈለቅናት መስለን መታየት አንችልም። እርሷ፡ ራሷን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፡ ፈጽማ ገሃድ አድርጋለች። እርሷም፡ አንዲት፥ ሌላ ወደር የሌላት፡ ያቺው አንዲት ብቻ ስለኾነች፡ እርሷን፡ በሥዕልም ኾነ በቅርጽ፡ ወይም በሌላ መልክ አስመስሎ፡ በምንም ዓይነት ማቅረብ አይቻልም።

ስለዚህ፡ ኹላችንም፡ ለዚያችው፡ ለአንዲቱ እውነት ብቻ ታማኞች መኾን፥ ራስዋንም ለእኛ ትገልጽልን ዘንድ፡ ወደእርሷ የሚያደርሰንን መንገድ በመሻት፡ በንጹሕ ትጋትና በልባዊ ጸሎት፡ ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርብናል። ከዚህ ብቅዓት ለመድረስ ግን፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም ፍቅር፡ በሰውነታችን ውስጥ ማደሪያን ያገኝ ዘንድ፡ በእኛ በኩል፡ የመንፈሳዊ ልቦናችንንና የሥጋዊ አእምሮአችንን ደጃፎች፡ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት፡ ክፍት ማድረግ፡ ተቀዳሚ ተግባራችን ይኾናል። ይህም ማለት፡ የተፈጥሮ ዝንባሌው፡ ክፋትና በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ መኾኑን፡ በግብሩ ያረጋገጠው፡ ሥጋዊ አእምሮአችን፡ የእኔነት ጽነት በተጠናወተው ፍትወቱ እየጸነሰ ከሚያመነጫቸው፡ የተለያዩ ዓለማውያን አስተሳሰቦች፡ ራሳችንን፡ አስቀድመን አጥርተንና አርቀን፡ በዚያ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ፡ ፈጽመን ልንጥለቀለቅ ይገባል ማለት ነው።

## መልሱ፡
## ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው!

እነሆ ዛሬ፡ እግዚአብሔር የቀጠራት፡ ያች ቀን በደረሰች ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ያለችው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ጠብቃ ስላቆየቻቸው ምሥጢራውያን ሀብታት የሚናገረው፡ የዘገየው የምሥራች ዜና፡ ይኸው፡ በወቅቱ ተገለጸ! ወደብርሃን ወጣ! "*የእግዚአብሔር እውነት፡* ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት የምትሰጠው ምስክርነት" በሚል አርእስት፡ በተዘጋጀ ጽሑፍ መልእክትም፡ ለእርስዎ ሳይቀር፡ እንዲደርስዎ ኾነ!

ያም መልእክት፡ ከሌሎቹ ቅዱሳት ምሥጢራት መካከል፡ ተሸፍኖ የኖረውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን እውነተኛ ማንነት፡ ገላልጦና በጽሑፍ አብራርቶ አቀረበው! ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ አርአያ ኾኖ፡ በቅድሚያ እንደታየው፡ እንደመልከ ጼዴቅ ኹሉ፡ እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስም፡ ከሦስቱ የኖኅ ልጆች፡ ማለትም፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች በመወለዱ፡ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊ መልክ ያለው የመኾኑን እውነታ ያረጋግጣል። ከዚህ የተነሣ ነው፡ አምላክ ሰው ኾኖ፡ ነጭ፥ ጥቁር፥ ቀይ እየተባባሉ፡ ጤናማ ባልኾነ ስሜት፡ ራሳቸውን ለያይተውና ከፋፍለው የሚኖሩትን፡ እኒህን፡ ሦስት፡ የሰው ትውልድ ዓበይት የዘር ሓረጎች፡ አስታርቆ፡ ለዘለዓለም ሊያዋህዳቸው የበቃው። ከዚህ ጋር፡ *"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የሚለው መለኮታዊው የማዕርግ ስያሜ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተሰጠ መኾኑን፡ ይኸው መልእክት በማያወላውል መልክ፡ አጠንክሮ ያረጋግጣል።

እንግዴህ፡ ይህን የምሥራች ዜና የሰማችሁባት ቀን፡ ለእናንተ፡ ታላቅ ሐሤት ልታደርጉባት የሚገባችሁ ልዩ ዕለት ናት። ምክንያቱም፡ የሕሊና ተምኔታችሁ ተሟልቶ የተፈጸመላችሁ መኾኑን፡ ይኸው፡ ራሳችሁ፡ ለራሳችሁ፡ የዓይን ምስክሮች ለመኾን በቃታችኋልና! ለፈጣሪያችሁ ስታቀርቡት ለኖራችሁት ጸሎትም፡ ይኸው መልስ አግኝታችኋልና! በጽኑ ምኞት የጓጓችሁበት ፍላጎታችሁም፡ ይኸው ተፈጽሞላችኋልና!

አዎን፥ ይህች ዕለት፡ እናንተና የቀደሙት አባቶቻችሁ፡ የእግዚአብሔርን ቃል በመከተል፡ ለዘመናት፡ ስትዋትቱበት የኖራችሁበትን የፍለጋ ጉዞ አከናውናችሁ፡ አማናዊዉ መሪያችሁ ማን እንደኾነ ታውቁት ዘንድ፡ ራሱን በገሃድ ከገለጠበት ማረፊያው የደረሳችሁባት ቀን ስለኾነች፡ በታላቅ ደስታ፡ ልታዘክሩዋት ይገባችኋል!

ባለፉት ኹለት ሺህ ዓመታት፡ *"እኔ በእውነት ልመሰክር፡ ስለዚህ ተወልጃለሁ! ስለዚህም ወደዓለም መጥቻለሁ! ከእውነት የኾነ ኹሉ ድምፄን ይሰማል!"* ብሎ የተናገረ፥ የመለኮትነት ባሕርይ ያለው፥ ሰው የኾነ አምላክ፥ ከይሁዳ ነገድ የተገኘና ድል አድራጊ የኾነ አንበሳ፥ የዳዊትና የቤትሳባ፥ የሰሎሞንና የማክዳ ዘር ኾኖ፡ በመጨረሻ፡ ከድንግል ማርያም የተወለደ፥ ስሙም፡ ኢየሱስ ተብሎ የተጠራ፥ የጽዮን ንጉሥ፥ የኢትዮጵያና እንዲሁም፡ በሰማይና በምድር፡ የፍጥረቱ ኹሉ ንጉሠ ነገሥት የኾነ፥ በዚህ ማንነቱም፡ በመላው ዓለም የሰው ዘር ዘንድ፡ በአብዛኛው ተቀባይነትን ያገኘ፡ እንዲህ ያለ ኢትዮጵያዊ መሢሕ፡ በፊታችን፡ በሕያውነት ቆሞ የሚገኝ ሲኾን፡ ታዲያ፡ እናንተ፡ ለምንድር ነው፡ ሌላ ኢትዮጵያዊን፡ አምላክ ለማድረግ የምትፈልጉት?

## በቍስል ላይ ቍስል

ለኢትዮጵያ፡ ዛሬ ያለባት ችግር አንሦ፡ ሌላ ተጨማሪ ጠንቅ፡ ልንፈጥርባት አይገባም! የተዘፈቀችበትና የተሸከመችው ይበቃታል! *"እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን፡ ሰው አይለየው"* የሚለው መለኮታዊ ቃል፡ በይፋ ክህደትና በዓመፅ ድፍረት ተሽሮ፡ በየምክንያቱና በየአስባቡ፡ ማለትም፡ በሃይማኖት ግላዊነት፥ በኅብረተሰብ አኗኗር፥ በአመራር ፖሊቲ፥ በሀብት ይዞታ፥ በጐሣ፥ በቋንቋና በብሔራዊ ክልል፥ እንዲሁም፡ ምሁራዊ፥ ቁሳዊና ግላዊ በኾኑ አስተሳሰቦች፡ እነሆ፡ ኢትዮጵያ፡ አካሏ እንዲገነጣጠል፥ ኢትዮጵያውያንም፡ እርስ በእርሳቸው እንዲለያዩ እየተደረገ ነው፡፡ ኢትዮጵያ፡ ለአካላዊው መገነጣጠልና ለመንፈሳዊው መለያየት፡ እንዲህ ባለ፡ የተጋለጠ ኹኔታ ላይ እንደምትገኝ እያወቅን፡ ለዚህ ችግር የዳረጓት፡ ክፋትና ጠላቶቿ፡ ኃይላቸው ሊጠናከር የሚችልበትን፡ ሌላ ተጨማሪ ድጋፍ፡ አምን፡ እኛ ልናበረክት አይገባም፡፡

አሁን፡ እኛ፡ በግል በተናጠል፡ ወይም በጋራ በመተባበር፡ ልናደርገው የሚያስፈልገን፥ ከእኛ የሚጠበቀውም፡ ኢትዮጵያን፡ በኹለንተና መልኳና ይዞታዋ፡ ማለትም፡ በሥጋዊውም ኾነ በመንፈሳዊው አቋሟ፡ የነበረ አንድነቷንና አማናዊ ማንነቷን መልሳ ለማግኘት ትችል ዘንድ፡ እንድንረዳትና እንድናግዛት ነው፤ ይህንንም ግዳጅ በተግባር ላይ ለማዋል፡ መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለደቀ መዛሙርቱና በእርሱ ላመኑት ኹሉ፡ ወደአባቱ፡ ወደእግዚአብሔር አብ በመጸለይ፡ *"አባት ሆይ! አንተ በእኔ እንዳለህ፥ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ፡ በእኛ አንድ ይኾኑ ዘንድ እለምናለሁ"* ሲል[፲፬]፡ ለተናገራቸው ቃላት፡ በቅድሚያ፡ ራሳችንን ማብቃት ይኖርብናል፡፡


እርስዎና እርስዎን የመሰሉት፡ ለኢትዮጵያ፡ በተለይም፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ ያላችሁ ፍቅር፡ የቱን ያህል የጸና መኾኑን፡ ዓለሙ ኹሉ፥ እኔ ጭምር፡ በዓይናችን እንመለከታለን፡፡ እንዲህ ከኾነ፡ ለኹለቱም ያላችሁን ፍቅርና አክብሮት፡ ለእኛና ለዓለሙ ኹሉ፡ እንደገና አረጋግጣችሁ፤ በገሃድ ለማሳየት፡ ይኸው፡ አሁን፡ መልካም ዕድል ቀርቦላችኋል፤ ይኸውም፡ ኢትዮጵያና ልጆቿ፡ አጼዎቿን ኹሉ ጨምሮ፥ መላ ሕይወታቸውን ሰጥተው ያገለገሏትን፡ የእግዚአብሔርን እውነት መቀበል ነው፡፡

በቅዱሱ ኪዳን ፍርድ፡ ጨልጠን እንድንጠጣው ተበይኖብን የተሰጠን፡ መራራ ጽዋ፡ ሞልቶ መፍሰሱ እንደቀጠለ መኾኑን ከቶ አይመለከቱምን? ታዲያ፥ በዚህ ጽዋ ላይ፡ ሌላ የመርዝ ጠብታ መጨመር አግባብና የሚያስፈልግ መስሎ ይታይዎታልን? እንግዴህ፡ ከዚህ ግብርዎ ተጸጽተውና ንስሓ ገብተው በመመለስ፡ *የእግዚአብሔር እውነት፡* በዚህ ረገድ የምትሰጠውን የምስክርነት ቃል ባይቀበሉ፡ ይህም ማለት፡ ይህንኑ የምስክርነት ቃሏን በመቃወም፡ አሁንም በያዙት አቋምዎ ጸንተው የሚቀጥሉበት ከኾነ፡ ቆርጠው የተነሡት፡ ኢትዮጵያንና አጼ ኃይለ ሥላሴን ከመጥቀም ይልቅ፡ ኾነ ብለው ለመጉዳት እንደኾነ፡ በገሃድ ተረጋግጦ ይታወቃል፡፡

በኢትዮጵያና በልጆቿ ፊት የደነቀሩት ችግር፡ ምን ዓይነት መኾኑን ለማስረዳት፡ "በቁስል ላይ ቁስል" የሚለውን የኢትዮጵያውያን የምሳሌ ቃል፡ እዚህ ላይ መጥቀስ አግባብ ይኾናል፡፡

## የዓለሙ መፋረጃ!

እንግዲህ፡ በእኔ በኩል፡ ለእርስዎና እርስዎን ለመሰሉት ኹሉ፡ በዓቅሜ፡ ላበረከት የሚገባኝ ምዕዳኔ፥ ምክሬ፡ በዚህ ያበቃል:: ከዚህ ተከታትሎ፥ ጥያቄዎን የሚመልሰውና ግራንጃዎን የሚያቃናው፡ ተገቢ ማብራሪያና የእውነት ማስረጃ፤ እነሆ፤ በመልክ በመልኩ ተዘርዝሮ ቀርቧልና በማስተዋል ይመልከቱት!



የቀድሞው "ቄስ"ና "መልአከ ሰላም"፥ የኋላው ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም፤ (ዝክረ ነገራቸው፥ በገጽ ፩፻፹፫-፩፻፹፬ እና ፪፻፷፯-፪፻፸ ይገኛል::)

የዓለሙ መፋረጃ!

እንግዴህ፡ በእኔ በኩል፡ ለእርስዎና እርስዎን ለመሰሉት ኹሉ፡ በዓቅሜ፡ ላበረክት የሚገባኝ ምዕዳኔ፥ ምክሬ፡ በዚህ ያበቃል:: ከዚህ ተከታትሎ፡ ጥያቄዎን የሚመልሰውና ግራንጃዎን የሚያቃናው፡ ተገቢ ማብራሪያና የእውነት ማስረጃ፡ እነሆ፡ በመልክ በመልኩ ተዘርዝሮ ቀርቧልና በማስተዋል ይመልከቱት!




የቀድሞው "ቄስ"ና "መልአከ ሰላም"፥ የኋላው ንቡረ እድ ድሜጥሮስ ገብረ ማርያም፤ (ዝክረ ነገራቸው፡ በገጽ ፩፻፹፫-፩፻፹፬ እና ፪፻፷፮-፪፻፸ ይገኛል::)

¡ቲኌጠቂመ ቖሯረኈጎህሂ
•ወሀሠሠቀኝ

፤ቲሀሂ ኈ•ፉሃሀመ
•ወሀ*ሃ7ቱ6 ሀጋቂሀ

፤ቲጎበሂ
•ወመሄ*ዓቱ6 ጋ•ወጠሀ ፡ፇሁ
ቲኣ•ወሂ ጋዋሀ•ሂችዘሬሂሀ





¡ፄ7ቅመ •መሀዕ6